بســـــــــــــم الله الرحـــــــــــيم

الحمد لله رب العالمين و صلى الله وسلم على سيدنا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين

مناسك الحج والعمرة باللغة الأمهرية (الأثيوبية) والعربية

# የሐጅና ዑምራ ሥራ አፈፃፀም ስርዓት በአማረኛና አረበኛ

## حكم الحج

الحج فرض عين على كل مكلف مستطيع في العمر مرة وهو ركن من أركام الإسلام وقد ثبتت فرضيته بالكتاب والسنة والإجماع

## የሐጅ ህግ(ብይን)

ሐጅን በሕይወት አንድ ጊዜ መፈፀም(ማድረግ) ለአካለ መጠን በደረሰና ችሎታ ባለዉ ሁሉ ግዴታ ነዉ ፡፡ ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ሲሆን ግደታነቱ በቁርዓን፣ በሀዲስና በዐሊሞች ስምምነት( ኢጅማዕ) የተረጋገጠ ነዉ ፡፡

## من فضائل الحج

1 . الحج يمحق الذنوب المتقدمة

فعن أبي هريرة أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال "من حج فلم يرفث ولم يفسق رجع كيوم ولدته أمه (متفق عليه)

2 . الحج سبب للعتق من النار

**فعن عائشة أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال "ما من يوم أكثر أن يعتق الله فيه عبدا من النار من يوم عرفة وإنه ليدنو ثم يباهى بهم الملائكة ( رواه مسلم)**

**3. الحج جزاؤه الجنة**

**فعن أبي هريرة أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال "العمرة إلى العمرة كفارة لما بينهما والحج المبرور ليس له جزاء إلا الجنة (متفق عليه)**

**4. الحج من أفضل الأعمال**

**فعن أبي هريرة أن رسول الله صلى الله عليه وسلم " سئل: أي الأعمال أفضل ؟ فقال: "إيمان بالله ورسوله "قيل ثم ماذا ؟قال "الجهاد في سبيل الله "قيل ثم ماذا؟قال "حج مبرور"(متفق عليه)**

## የሐጅ ትሩፋት

1. ሐጅ ያለፉ ወንጀሎችን ይሰርዛል፡፡

አቡ-ሁረይራ ﵁ እንዳስተላለፉት ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል ፡-ሐጅ ያደረገ ከሚስቱ ጋርም ያልተገናኘና (ሌሎች ከሴቶች የሚከጀሉ ስሜታዊ ጉዳዮችን ያልፈፀመ)እንዲሁም ወንጀል ያልሠራ እናቱ እንደወለደችው ዕለት ሆኖ (ከኃጢአት ፀድቶ) ይመለሳል፡፡(ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

2. ሐጅ ከእሳት ነፃ ለመሆን ሰበብ ነዉ፡፡

አዒሻ ስራዋን አላህ ይውደድላትና

እንዳወሳችዉ ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል ፡-አላህ ባሪያዉን ከእሳት ነፃ የሚያወጣበትና የቀረበ ሆኖ መላይኮችን የሚፎካከርበት የሆነ እንደ አረፋ ቀን የለም ፡፡ (ሙስሊም የዘገቡት)

3. ሐጅ ዋጋዉ ጀነት ብቻ ነዉ፡፡

አቡ-ሁረይራ ﵁ እንዳስተላለፉት ረሱል ﷺእንዲህ ብለዋል፡- የዑምራ (ሥነ-ሥርዓት መፈፀም )ከአንድ ዑምራ እስከ ቀጣዩ ዑምራ በመካከላቸዉ የሚፈፀመዉን ወንጀል ያስፍቃል ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ዋጋዉ ጀነት ብቻ ነዉ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

4. ሐጅ ትልቅ ትሩፋት ካላቸዉ ስራዋች አንዱ ነዉ፡፡

አቡ-ሁረይራ ﵁ እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺከስራዋች ሁሉ ትልቅ ትሩፋት ያለዉ ስራ የትኛዉ ነዉ በማለት ተጠየቁ፡፡ በአላህና በመልዕክተኛዉ ማመን ነዉ ሲሉ መለሱ፡፡ በመቀጠልስ ምን ? በአላህ መንገድ ላይ መዋጋት አሉ:: ተጨማሪም ተጠየቁ ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ብለዉ መለሱ፡፡ ((ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

**شروط الحج**

**إن الشريعة الإسلامية جاءت من لدن حكيم خبير،لايشرع منها إلا ما كان موافقا للحكمة ،ومطابقا للعدل،لذلك كانت الواجبات والفرائض لا تلزم الخلق إلا بشروط مرعية يلزم وجودها حتى يكون فرضها واقعا موقعه .**

**فمن ذلك فريضة الحج لا تكون فرضا علي العباد إلا بشروط:**

## <u>የሐጅ መስፈርቶች(ደንቦች)</u>

ማንኛዉም የኢስላም ህግ የመጣዉ ሚስጥሮችን ሁሉ ጠንቅቆ አዋቂና ጥበበኛ ከሆነዉ (ከአላህ)ዘንድ ነዉ፡፡ ስለዚህ ከጥበቡና ከፍትሁ ጋር የሚስማማን ፣ የሚዛመድን ህግ እንጅ አይደነግግም ለዚህም ነዉ ዋጅባትና ፈራኢዶች(ግዴታዎች) መሟላት ያለባቸዉ ደንቦች ካልተሟሉ በሰዎች ላይ ግዳጅ

የማይሆኑት  ግዳጅ የሆነዉ ነገር እቦታዉ ላይ  ማረፍ ስላለበት፡፡  የሐጅን ግዴታ ብንመለከት  በሰዎች ላይ ግዴታ የሚሆነዉ ደንቦች ሲሟሉ ብቻ ነዉ፡፡

**الشرط الأول : أن يكون مسلما ، بمعنى أن الكافر لا يجب عليه الحج قبل الإسلام، وإنما نأمره بالإسلام أولا ، ثم بعد ذلك نأمره بفرائض الإسلام ،لأن الشرائع لا تقبل  إلا بالإسلام،قال الله تعالي [وما منعهم أن تقبل منهم نفقاتهم إلا أنهم كفروا بالله وبرسوله ولا يأتون الصلاة إلا وهم كسالى ولا ينفقون إلا وهم كارهون ] التوبة.54**

* የመጀመሪያዉ መስፈርት ሙስሊም መሆን ነዉ :: ከሃዲ ከመስለሙ በፊት ሐጅ ግዴታ አይሆንበትም ::  መጀመሪያ ኢስላምን እንዲቀበል  ይታዘዛል ከዚህ በኃላ ኢስላም ግደታ ያደረጋቸዉን በሙሉ መፈፀም እንዳለበት እናስረዳዋለን :: ምክኒያቱም  ህጎች ያለ ኢስላም  ተቀባይነት ስለሌላቸዉ፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-( የለገሱት (ሃብት)ተቀባይነት እንዳይኖረዉ  እንቅፋት የሆነዉ  በአላህና በመልዕክተኛዉ በመካዳቸዉ፣ ሶላትን እየተሰላቹ እንጅ የማይሰግዱ፣ እየጠሉ እንጅ የማይለግሱ በመሆናቸዉ ነዉ)  (አት-ተዉበህ54)፡፡

**الشرط الثاني : العقل ،فالمجنون لا يجب عليه الحج ولا يصح منه لأن الحج لابد فيه من نية وقصد ،ولا يمكن وجود ذلك من المجنون .**

* ሁለተኛዉ መስፈርት  ጤናማ አዕምሮ ነዉ ፡፡ የአዕምሮ ችግር ያለበት ሰው  የሐጅ ግዴታ የለበትም፡፡  ሐጅ ቢያደርግ

ተቀባይነት የለዉም ምክኒያቱም ሐጅ ኒያ ያስፈልገዋል ኒያ ደግሞ የአዕምሮ ችግር ካለበት ሊገኝ አይችልም፡፡

الشرط الثالث : البلوغ ويحصل البلوغ في الذكور بواحد من أمور ثلاثة

* الإنزال أي إنزال المني لقوله تعالي (وإذا بلغ الأطفال منكم الحلم فليستأذنوا كما استأذن الذين من قبلهم) (سورة النور59) وقول النبي صلي الله عليه سلم "غسل الجمعة واجب علي كل محتلم "متفق عليه .

* نبات شعر العانة وهو الشعر الخشن ينبت حول القبول لقول عطية القرظي رضي الله عنه. عرضنا علي النبي صلي الله عليه وسلم يوم قريظة فمن كان محتلما أو أنبت عانته قتل ومن لا ترك [رواه أبو داود]

* تمام خمس عشرة سنة لقول عبد الله بن عمر رضي الله عنهما عرضت علي النبي صلي الله عليه وسلم يوم أحد وأنا ابن أربع عشرة سنة فلم يجزني. وعرضت عليه يوم الخندق وأنا ابن خمسة عشرة سنة فأجازني.

* ويحصل البلوغ في الإناث بما يحصل به البلوغ في الذكور وزيادة أمر رابع وهو الحيض فمتى حاضت فقد بلغت وإن لم تبلغ عشر سنين

فلا يجب الحج علي من دون البلوغ لصغر سنه وعدم تحمله أعباء الواجب ولقول النبي صلي الله عليه وسلم "رفع القلم عن ثلاثة عن النائم حتى يستيقظ وعن الصغير حتى يكبر وعن المجنون حتى يفيق" رواه أحمد وأبو داود والنسائي لكن يصح الحج من الصغير الذي لم يبلغ لحديث بن عباس رضي الله عنهما أن النبي صلي الله عليه وسلم لقي ركبا بالروحاء –

اسم موضع- فقال"من القوم؟" قالوا المسلمون فقالوا من أنت؟قال "رسول الله"

فرفعت إليه امرأة صبيا فقالت ألهذا حج؟ قال: "نعم ولك أجر"رواه مسلم.

*ሶስተኛዉ መስፈርት ለአካለ መጠን መድረስ ነዉ፡፡

ወንዶች አካለ መጠን ለመድረስ ከሶስት ምልክቶች አንዱ ብቻ መገኘቱ በቂ ነዉ፡፡

1. የዘር ፈሳሽ ማፍሰስ አላህ እንዲህ ብሏል፡-(ግና ከናንተ ዉስጥ ሕጻናት ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ እነዚያ ከነርሱ በፊት የነበሩት (ታላላቆች) እንዳስፈቀዱት እነርሱም ያስፈቅዱ) (አን-ኑር59)፡፡ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-( ጁሙዓ ቀን መታጠብ ላቅመ አዳም (ሔዋን)በደረሰ ሰዉ ሁሉ ላይ ግዴታ(ዋጅብ) ነዉ)፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

2.የብልት ፀጉር ማብቀል ፡- ዐጢያ አልቁረዚ ﵁ እንዲህ ብለዋል፡- የቁረይዟ ቀን ነቢዩ ዘንድ ቀረብን አካለ መጠን የደረሰ ወይም ብልቱ ላይ ፀጉር ያበቀለ ተገደለ ግን ከዚህ ሌላ የሆነ ይቅርታ ተደረገለት፡፡

3. አስራ አምስት ዓመት መሙላት፡- አብደላ ኢብኑ ኡመር﵁ እንዳወሱት የዑሁድ ዕለት ነቢዩ ዘንድ እንዲቀርብ ታዘዝኩኝ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ስለነበርኩ ከለከሉኝ ኸንደቅ ጦር ላይ ግን የአስራ አምስት አመት ወጣት ስለነበርኩ ፈቀዱልኝ ብሏል፡፡

4. ሴት ልጆች አካለ መጠን ለመድረስ ለወንዶች የተሰጡ ምልክቶችና ተጨማሪ አራተኛ ምልክት አለ እሱም የወር አበባ ማየት ነዉ የወር አበባ ባየች ጊዜ አስር ዓመት ባይሞላትም እንኳ ለአቅመ አዳም በእርግጥ ደርሳለች ፡፡ ስለዚህ አካለ መጠን ያልደረሰ ዕድሜዉ ዝቅተኛ ስለሆነና የሐጅ ግዴታዋችን መሸከም (መተግበር) ስለማይችል ሐጅ

ግደታ አይሆንበትም፡፡ ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል፡- (ብዕር [1] ከሶስት ነገሮች ላይ ተነስቷል የተኛ ከእንቅልፉ እስከሚነሳ፣ ህፃን አካለ መጠን እስከሚደርስ እና ያበደ ከበሽታው እስከሚድን ድረስ )፡፡ ነገር ግን የህፃን ልጅ ሐጅ ተቀባይነት አለው፡፡ ኢብኑ አብባስ ﷺ እንዳወሱት ነቢዩ ﷺ አንድ ጊዜ ረውሃዕ እሚባል አካባቢ ላይ ሰዎችን አገኙ እናንተ እነማን ናችሁ አሏቸዉ ? እነሱም እኛ ሙስሊሞች ነን አሉ፡፡ እነሱም ለመሆኑ አንተ ማነህ ብለዉ ጠየቁ ? እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ በማለት መለሱ ከመካከላቸዉ አንዲት ሴት ህፃን ልጇን ከፍ አድርጋ በመያዝ ይህ ህፃን ሐጅ ቢያደርግ ሐጁ ተቀባይነት ይኖረዋልን በማለት ጠየቀች፡፡ መልዕክተኛዉም አዎ እንዴታ ሐጁ ትክክል ነዉ አንቺም ከአላህ አጅር ታገኛለሽ በማለት መልስ መለሱላት፡፡(ሙስሊም የዘገቡት)

**الشرط الرابع الحرية فلا يجب الحج علي مملوك لعدم استطاعته**

*አራተኛዉ መስፈርት ከባርነት ነፃ መሆን ነዉ፡፡ ከባርነት ነፃ ካልሆነ አቅም ስለሌለዉ ሐጅ ግዴታ አይሆንበትም ፡፡

**الشرط الخامس الاستطاعة بالمال والبدن بأن يكون عنده مال يتمكن به من الحج ذهابا وإيابا ونفقة ويكون هذا المال فاضلا عن قضاء الديون والنفقات الواجبة عليه وفاضلا عن الحوائج التي يحتاجها من المطعم والمشرب والملبس والمنكح والمسكن وما يحتاج إليه من مركوب وكتب علم وغيرها لقوله تعالي (ولله علي الناس حج البيت من استطاع إليه سبيلا) (آل عمران 97)**

---

[1] ህፃን ፣ እብድና የተኛ ሰው የሚፈፅሟቸው ስህተቶች አይፃፉባቸውም አላህም አይጠይቃቸዉም ፡፡

*አምስተኛዉ መስፈርት  አካላዊ እና ቁሳዊ አቅሙ የተሟላለት ሐጅ ለማድረግ  ሲሄድና ሲመጣ እንዲሁም ለተለያዩ ወጮች የሚያወጣዉ በቂ ገንዘብ ያለዉ መሆን፡፡ እዳዎች ካሉበት  እዳዎቹን ከከፈለ በኃላ  ከተለያዩ ግዴታ ከሆኑ ወጮችና አስፈላጊ  ጉዳዮቹ  የተረፈ መሆን ለምሳሌ፡- ከሚመገብበት፣ ከሚጠጣበት፣ ከሚለብስበት ከሚያገባበት፣ ከሚቀመጥበት፣ ከሚጋልበዉ የተረፈ እንዲሁም እዉቀትን ያዘሉ መፅሀፎችና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮቹን ካሟላ በኃላ  የሚተርፍ ገንዘብ መኖር አለበት፡፡  አላህ እንዲህ ብሏል፡-(ቤቱን ወደርሱ መጓዝ ለሚችሉ ሁሉ ይጎበኙ ዘንድ  አላህ በሰዎች ላይ ግዴታ አድርጓል )(አሊ ዒምራን 97)፡፡

ومن الاستطاعة أن يكون للمرأة محرم فلا يجب أداء الحج علي من لا محرم لها لا متناع السفر عليها شرعا إذ لا يجوز للمرأة أن تسافر للحج ولا غيره بدون محرم سواء كان السفر طويلا أم قصيرا وسواء كان معها نساء أم لا وسواء كانت  شابة جميلة أو عجوزا شوهاء وسواء في طائرة أم غيرها لحديث ابن عباس رضي الله عنهما أنه سمع النبي صلي الله عليه وسلم يخطب يقول "لا يخلون رجل بامرأة إلا ومعها ذو محرم ولا تسافر المرأة إلا مع ذي محرم "فقام رجل فقال يا رسول الله  إن امرأتي خرجت حاجة وإني اكتتبت في غزوة كذا وكذا فقال النبي صلي الله عليه سلم "انطلق فحج مع امرأتك"متفق عليه

ولم يستفصله النبي صلي الله عليه وسلم هل كان معها نساء أم لا ؟ولا هل كانت شابة جميلة أم لا؟ولا هل كانت آمنة أم لا؟

ሴትን በተመለከተ አብሮአት የሚሄድ ዘመድ (መህረም) መኖሩ መጓዝ ለሚችሉ ከሚለዉ ይገባል፡፡ ዘመድ የሌላት ሴት በኢስላም ህግ (ሸሪዓ)መሰረት መንገድ መጓዝ ክልክል ስለሆነ ሐጅ ግዴታ አይሆንባትም፡፡ ሴት ሐጅ ለማድረግም ይሁን ለሌላ ጉዞዉ አጭርም ይሁን ረዝርም ከሷ ጋር ሴቶች ቢኖሩም ባይኖሩም ዉበት ያላት ወጣት ብትሆንም ዉበት የሌላት አሮጊት በአዉሮፕላን ቢሆንም በሌላ ነገር ያለዘመድ ጉዞ አይፈቀድላትም ፡፡ ኢብኑ አብባስ ﵁ እንዳወሱት ረሱል ﷺ ሲመክሩ (ኹጥባ) ሲያደርጉ ሰምቻለሁ (ማንኛዉም ወንድ ከዘመዷ ጋር ካልሆነ በስተቀር ከሴት ጋር ማግለል አይፈቀድለትም ፡፡ ሴትም ከዘመዷ ጋር ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉንም ጉዞ መጓዝ አትችልም ብለዉ ሲናገሩ አንድ ሰዉ ቆመና የአላህ መልእክተኛ ሆይ ባለቤቴ(ሚስቴ) ሐጅ ለማድረግ ከቤት ወጥታለች እኔ ደግሞ ለጦር (ለጂሃድ) ተመዝግቢያለሁ ሲል አማከራቸዉ ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ከባለቤትህ ጋር ተጓዝና ሐጅ አድርግ በማለት መልስ መለሱለት)፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት) ከሴቶች ጋር ነዉ የምትጓዘዉ ወይስ ብቻዋን ፤ ዉበት ያላት ቆንጆ ናት ወይስ አይደለችም ፤ ታማኝ ናት ወይስ አይደለችም ብለዉ የአላህ መልዕክተኛ በዝርዝር የጠየቁት ነገር የለም፡፡

**والحكمة في منع المرأة من السفر بدون محرم صون المرأة عن الشر والفساد وحمايتها من أهل الفجور والفسق فإن المرأة قاصرة في عقلها وتفكيرها والدفاع عن نفسها وهي مطمع الرجال فربما تخدع أو تقهر فكان من الحكمة أن تمنع من السفر بدون محرم يحافظ عليها ويصونها ولذلك يشترط أن يكون المحرم بالغا عاقلا فلا يكفي المحرم الصغير أو المعتوه**

ኢስላም ሴትን ያለ ዘመድ ጉዞ ከመጓዝ የከለከለበት ጥበቡ(ሚስጥሩ) የተለያዩ ወንጀለኞች፣ አመፀኞች፣የብክለትና የተንኮል ባለቤቶች እንዳይዳፈሯት(የነርሱ ስሜት ማራገፊያ እንዳትሆን )ክብሯንና ደህንነቷን ለመጠበቅ ነዉ ። ሴት በተፈጥሮዋ ግንዛቤ ላይ እና ለህይወቷ በመከላከል ዙሪያ ድክመት ስላለባት ። ወንዶችም በጣም ስለሚፈልጓት ልትታለልና ልትሸነፍ ትችላለች ። እሚጠባበቃትና እሚከታተላት ዘመድ ሳይኖራት ጉዞ የተከለከለችበት ምክንያቱና ጥበቡ ይህ ነዉ። ለዚህም ነዉ አብሯት የሚጓዘዉ ዘመድ ለአካለ መጠን የደረሰና የአዕምሮ ባለቤት መሆን አለበት ተብሎ መስፈርት የተደረገዉ ። ለአካለ መጠን ያልደረሰ ዘመድና ቂል (ሞኝ) መህረም ለመሆን በቂ አይደለም ።

والمحرم زوج المرأة وكل ذكر تحرم عليه تحريما مؤبدا بقرابة أو رضاع أو مصاهرة.

*ዘመድ የሚባሉት ባለቤቷና የስጋም ሆነ የጡት ዘመድ ወይም በጋብቻ ምክኒያት ምንጊዜም እሷን ማግባት ክልክል የሚሆንበት ሰዉ ማለት ነዉ።

فالمحارم من القرابة سبعة :

1. الأصول وهم الآباء والأجداد وإن علوا سواء من قبل الأب أو من قبل الأم
2. الفروع وهم الأبناء وأبناء الأبناء وأبناء البنات وإن نزلوا
3. الإخوة سواء كانوا إخوة أشقاء أم لأب أم لأم .

4. الأعمام سواء كانوا أعماما أشقاء أم لأب أم لأم وسواء كانوا أعماما للمرأة أو لأحد من آبائها أو أمهاتها فإن عم الإنسان عم له ولذريته مهما نزلوا.

5. الأخوال سواء كانوا أخوالا أشقاء أم لأب أم لأم وسواء كانوا أخوالا للمرأة أو لأحد من آبائها أو أمهاتها فإن خال الإنسان خال له ولذريته مهما نزلوا.

6. أبناء الإخوة وأبناء أبنائهم وأبناء بناتهم وإن نزلوا سواء كانوا أشقاء أم لأب أم لأم

7. أبناء الأخوات وأبناء أبنائهم وأبناء بناتهن وإن نزلوا سواء كن شقيقات أم لأب أم لأم

## የስጋ ዘመድ የሚባሉት ሰባት ናቸዉ

1. መሰረት የሆኑ ዘመዶች አሉ እነሱም፡- አባቶችና አያቶች ደረጃቸዉ ከፍ ሚልም፡- በአባትም በዕናትም በኩል ያሉት ተመሳሳይ ናቸዉ፡፡

2. ቅርንጫፍ የሆኑ ዘመዶችም አሉ እነሱም፡- ወንድ ልጆችና የወንድ ልጆች ወንድ ልጆቻቸዉና የሴት ልጆች ወንድ ልጆቻቸዉ ናቸዉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም (ወደ ታች ቢወርዱም)

3 . ወንድሞች በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ ፡፡

4. የአባት የሆኑ አጎቶች አጎትነታቸዉ በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ አጎትነታቸዉ ለሴቷ ቢሆኑም ወይም ለአባቶቿና

ለእናቶቿ ተመሳሳይ ነዉ ምክኒያቱም ለአንድ ሰዉ አጎት ከሆነ ለዝርያዎቹ በሙሉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም አጎታቸዉ ይሆናል፡፡

5. የእናት የሆኑ አጎቶች አጎትነታቸዉ በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ አጎትነታቸዉ ለሴቷ ቢሆኑም ወይም ለአባቶቿና ለእናቶቿ ተመሳሳይ ነዉ ፡፡ምክኒያቱም ለአንድ ሰዉ አጎት ከሆነ ለዝርያዎቹ በሙሉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም አጎታቸዉ ይሆናል፡፡

6. የወንድሞች ወንድ ልጆቻቸዉና እንዲሁም ወንድ ልጆቻቸዉ ፤ የወንድሞች ሴቶች ልጆቻቸዉ ወንዶች ልጆቻቸዉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም ወንድምነታቸዉ በአባትና በእናት ብቻ የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ ፡፡

7. የእህቶች ወንድ ልጆቻቸዉና የወንድ ልጆቻቸዉ ወንድ ልጆች ፤ እንዲሁም የእህቶች ሴቶች ልጆቻቸዉ ወንዶች ልጆች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም እህትነታቸዉ በአባትና በእናትብቻ የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ፡፡

**والمحارم من الرضاع نظير المحارم من النسب لقول النبي صلي الله عليه وسلم يحرم من الرضاع ما يحرم من النسب . متفق عليه**

የጡት ዘመዶች ከስጋ ዘመዶች ጋር ተመሳሳይ ናቸዉ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል ፡-( በስጋ ዘመዶች ላይ ክልክል የሆነ ማንኛዉም ነገር በጡት ዘመዶች ላይ ክልክል ነዉ)፡፡

**والمحارم بالمصاهرة أربعة :**

1. **أبناء زوج المرأة وأبناء أبنائه وأبناء بناته وإن نزلوا.**

2. أباء زوج المرأة وأجداده من قبل الأب أو من قبل الأم وإن علوا.

3. أزواج بنات المرأة وأزواج بنات أبنائها وأزواج بنات بناتها وإن نزلن.

وهذه الأنواع الثلاثة تثبت المحرمية فيهم بمجرد العقد الصحيح علي الزوجة وإن فارقها قبل الخلوة والدخول .

4. أزواج أمهات المرأة وأزواج جداتها وإن علوا سواء من قبل الأب أو من قبل الأم لكن لا تثبت المحرمية في هؤلاء إلا بالوطء وهو الجماع في نكاح صحيح فلو تزوج امرأة ثم فارقها قبل الجماع لم يكن محرما لبناتها وإن نزلن.

__በጋብቻ ምክኒያት ዘመድ ሊሆኑ የሚችሉት አራት ናቸዉ__

1. ሚስት የባሏ ወንድ ልጆች ፣የወንድ ልጆቹ ወንድ ልጆች እንዲሁም የሴት ልጆቹ ወንድ ልጆች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም

2. ሚስት የባሏ አባቶችና አያቶች በአባት ወይም በእናት በኩል ቢሆኑ እንዲሁም ደረጃቸዉ ከፍ ቢልም

3. ማንኛዋም ሴት የሴት ልጆቿ ባሎች፣ የወንድ ልጆቿ ሴት ልጆች ባሎች እና የሴት ልጆቿ ሴት ልጆች ባሎች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም እነኝህ ሶስት ዘርፎች በሚስት ላይ ትክክለኛ የሆነ ጋብቻ በመፈፀሙ ብቻ

ባል ከሚስቱ ጋር ከማግለሉና ግንኙነት ከመፈፀሙ በፊት ቢፈታትም እንኳ ዝምድናቸዉ ይፀድቃል

4. ሴቶች የእናቶቻቸዉ ባሎች ፣የአያቶቻቸዉም ባሎች በደረጃ ከፍ ቢሉም በአባት በኩል ቢሆኑም እንዲሁም በእናት ነገር ግን እነዚህ ላይ ትክክለኛ በሆነ ጋብቻ መልክ ግንኙነት የፈፀሙ ካልሆነ ዝምድናቸዉ አይፀድቅም ስለዚህ

አንድ ሰዉ ሴት ቢያገባ ነገር ግን ግንኙነት ሳይፈፅም ቢፈታት ለሴት ልጆቿ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም ዘመድ ሊሆን አይችልም

فإن لم يكن الإنسان مستطيعا بماله فلا حج عليه، وإن كان مستطيعا بماله عاجزا ببدنه نظرنا . فإن كان عجزا يرجى زواله كمرض يرجى أن يزول انتظر حتى يزول ،ثم يؤدى الحج بنفسه. وإن كان عجزا لا يرجى زواله ،كالكبر والمرض المزمن الذي لا يرجى برؤه ،فإنه ينيب عنه من يقوم بأداء الفريضة عنه لحديث ابن عباس رضي الله عنهما

أن امرأة من خثعم قالت "يا رسول الله إن أبي أدركته فريضة الله في الحج شيخا كبيرا لا يستطع أن يستوي علي ظهر بعيره ،قال حجي عنه"رواه الجماعة هذه شروط الحج التي لا بد من توافرها لوجوبه .

واعتبارها مطابق للحكمة والرحمة والعدل (ومن أحسن من الله حكما لقوم يوقنون)

በቂ ገንዘብ የሌለዉ ሀጅ ማድረግ ግደታ አይሆንበትም ነገር ግን በቂ ገንዘብ እያለዉ የአቅም ድክመት ካለበት ድክመቱ ምን እንደሆነ መመልከት አለብን ፡፡ ድክመቱ ሊወገድ የሚችል ከሆነ ይወገዳል ተብሎ ተስፋ የሚደረግ በሽታን ይመስል በሽታዉ እስከሚያገልልህ ድረስ ጠብቅ(ታገስ) ይባላል፡፡ ከዚያም ከበሽታዉ ሲድን የሀጅን ስራዎች ራሱን ችሎ መስራት አለበት፡፡ ድክመቱ ይወገዳል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ እርጅናና ይድናል ተብሎ ተስፋ የማይደረግለት በሽታን ይመስል ግዴታ የሆነበትን ሐጅ እሱን ወክሎ የሚሰራለትን ሰዉ ይተካ፡፡ ኢብኑ አብባስ ﵁ እንዳወሱት ኸስአም ከሚባል ጎሳ አንድት ሴት የአላህ

መልዕክተኛ ሆይ እግመሉ ጀርባ ላይ ተስተካክሎ መቀመጥ በማይችልበት ሁኔታ በጣም ትልቅ ሽማግሌ በሆነበት ሰዓት አባቴን የሐጅ ግዴታ አገኘዉ ምን ማድረግ አለበት በማለት ጠየቀች፡፡ መልዕክተኛዉም እሱን (አባትሽን)ተክተሽ አንቺ ሐጅ አድርጊ በማለት መልስ መለሱላት፡፡

**هذه شروط الحج التي لابد من توافرها لوجوبه واعتبارها مطابق للحكمة والرحمة والعدل ( ومن أحسن من الله حكما لقوم يوقنون ) (المائدة 50)**

እነኝህ መስፈርቶች ሐጅ ግዴታ ይሆን ዘንድ መሟላት ያለባቸዉ ናቸዉ፡፡ እነኝህ መስፈርቶች መገምገማቸዉ ከአላህ ጥበብ ፣ እዝነትና ፍትህ ጋር የሚስማማ ነዉ አላህ እንዲህ ብሏል(ፅኑ እምነት ላላቸዉ ሰዎች በፍርድ ከአላህ የተሻለ ማን ነዉ?)( አል-ማኢደህ 50)

**المواقيت وأنواع الأنساك**

**المواقيت نوعان : زمانية ومكانية**

**فالزمانية للحج خاصة أما العمرة فليس لها زمن معين لقوله تعالي ( الحج أشهر معلومات ) وهي ثلاثة شوال وذو القعدة وذو الحجة .**

## ስለ ሐጅ ስራ አፈፃፀም ስርዓቶችና ስለ ኢህራም ክልሎች

የኢሕራም ክልሎች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ጊዜን የሚመለከት እንዲሁም ቦታን የሚመለከት ፡፡

* ጊዜን የሚመለከተዉ ከሐጅ ጋር ብቻ የተሳሰረ ነዉ ዑምራ ለማድረግ የጊዜ ገደብ የለዉም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡- (የሐጅ ጊዜ የታወቁ ወራት ናቸዉ ) እነሱም ሶስት ናቸዉ ሸዋል፣ ዙል ቂዕዳና ዙል ሒጃ በመባል ይታወቃሉ፡፡

وأما المكانية فهي خمسة وقتها رسول الله ففي الصحيحين من حديث ابن عباس رضي الله عنهما قال "وقت رسول الله صلي الله عليه وسلم لأهل المدينة ذا الحليفة ،ولأهل الشام الجحفة، ولأهل نجد قرن المنازل، ولأهل اليمن يلملم، فهن لهن ولمن أتي عليهن من غير أهلهن لمن كان يريد الحج والعمرة فمن كان دونهن فمهله من أهله وكذلك حتى أهل مكة يهلون منها

وعن عائشة رضي الله عنها أن النبي صلي الله عليه وسلم وقت لأهل العراق (ذات عرق) رواه أبو داود والنسائي .

* ሌላዉ ቦታን የሚመለከት ነዉ  እነሱም፡- አምስት/5/ ናቸዉ ነቢዩ ﷺ የከለሏቸዉ የሆኑ  ኢብኑ አብባስ ﷽ እንዳወሱት ረሱል ﷺ ለመዲና ህዝቦች ዙል ሑለይፋህ ለሻም ህዝቦች አልጁህፋህ ፣ ለነጅድ ህዝቦች ቀርነል መናዚል  እና ለየመን ህዝቦች የለምለምን የኢህራም  ክልል  አድርገዋል ፡፡ እነኝህ ክልሎች  አሁን ስማቸዉ ለተጠቀሱት ህዝቦችና ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልሎች (ሚቃቶች)ናቸዉ፡፡ መኖሪያቸዉ ከሐረም ክልል ዉጪ ከሚቃት ክልሎች ዉስጥ ያሉ ከተሞች( እንደ ጅዳ የመሳሰሉት አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች) ኢሕራም የሚያደርጉት ባሉበት ቦታ ሲሆን ሚቃታቸዉ መኖሪያቸዉ ነዉ፡፡   የመካ ከተማ  ነዋሪዎች ሐጅ ለማድረግ  ከቤታቸዉ ኢህራም  ያድረጉ  ፡፡( ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)       አዒሻ አላህ ይዉደድላትና  ነቢዩ ﷺ ለኢራቅ ህዝቦች ዛቱ ኢርቅ የሚባል ክልል አድርገዋል ፡፡ (አቡዳዉድና ነሳዒ የዘገቡት)

**فالأول :ذو الحليفة ويسمي (أبيار علي) بينه وبين مكة نحو عشر مراحل وهو ميقات أهل المدينة ومن مر به من غيرهم**

* የመጀመሪያዉ ዙል ሑለይፋ (አብያር አሊይ) ተብሎ ይጠራል ፡፡ በመካ ከተማና በዙልሑለይፋ መካከል አሥር መራሂሎች ይገኛሉ (450 ኪ.ሜ) የመዲና ሰዎች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች

**الثاني الجحفة وهي قرية قديمة بينها وبين مكة نحو ثلاث مراحل وقد خربت فصار الناس يحرمون من رابغ بدلا عنها وهي ميقات اهل الشام ومن مر بها من غيرهم إن لم يمروا بذي الحليفة قبلها فإن مروا بها لزمهم الإحرام منها.**

* ሑለተኛዉ አል ጁህፋ ይባላል የቆየች የዱሮ ከተማ ስለነበረች ፈራርሳለች በእሷና በመካ ከተማ መካከል ሶስት መራሂሎች ይገኛሉ (183 ኪ.ሜ) ራቢግ እሚባል ቦታ ላይ በጁህፋ ለዉጥ የሻም ሰዎችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ ነገር ግን በዙል ሑለይፋ ላይ ካለፉ ዙልሑለይፋ ላይ ኢህራም ማድረግ ግደታ ይሆንባቸዋል ፡፡

**الثالث قرن المنازل ويسمي (السيل)بينه وبين مكة نحو مرحلتين وهو ميقات أهل نجد ومن مر به من غيرهم .**

* ሶስተኛዉ ቀርነል መናዚል ይባላል (አሰይል ) ተብሎም ይጠራል በእሱና በመካ ከተማ መካከል ሁለት መራሂሎች ይገኛሉ(75 ኪ.ሜ) የነጅድ ሰዎችና እንዲሁም በነሱ በኩል

አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ፡፡

**الرابع يلملم وهو جبل أو مكان بتهامة بينه وبين مكة نحو مرحلتين**

**ويسمي (السعدية )وهو ميقات أهل اليمن ومن به من غيرهم**

* አራተኛዉ የለምለም ይባላል ቲሃማህ በሚባል አካባቢ የሚገኝ የተራራ ወይም የቦታ ስም ነዉ በመካና በየለምለም መካከል ሁለት መርሃላዎች ይገኛሉ (92 ኪ.ሜ) (አስ ሰዕዲያ )ተብሎም ይጠራል ፡፡ ለየመን ህዝቦችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ፡፡

**الخامس : ذات عرق ويسمي عند أهل نجد (الضريبة )بينها وبين مكة**

**مرحلتان وهي لأهل العراق ومن مر بها من غيرهم**

*አምስተኛዉ ዛቱ ኢርቅ ይባላል የነጅድ ሰዎች( አዶሪበህ) ብለዉ ይጠሩታል በመካና በዛቱ ኢርቅ መካከል ሁለት መርሃላዎች ይገኛሉ(94 ኪ.ሜ) ለኢራቅ ህዝቦችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ፡፡

**ومن كان أقرب إلي مكة من هذه المواقيت فميقاته مكانه فيحرم منه، حتى أهل مكة يحرمون من مكة إلا في العمرة فيحرم من كان في الحرم من أدني الحل لأن النبي صلي الله عليه وسلم قال لعبد الرحمن بن أبي بكر "اخرج بأختك – يعني عائشة لما طلبت منه العمرة – من الحرم فلتهل بعمرة" (متفق عليه)**

መኖሪያቸዉ ከሐረም ክልል ዉጪ ከሚቃት ክልሎች ዉስጥ ያሉ ከተሞች ኢሕራም የሚያደርጉት ባሉበት ቦታ ሲሆን

ሚቃታቸዉ መኖሪያቸዉ ነዉ፡፡ የመካ ከተማ ነዋሪዎች ሐጅ ለማድረግ ከቤታቸዉ ኢህራም ሲያደርጉ ዑምራ ለማድረግ ግን ከሐረም ክልል ዉጭ ተንዒም ሄደዉ ኢህራም ያድርጉ ነበዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ለአቡ በክር ልጅ አብደረህማን ለሚባለዉ አኢሻ ዑምራ ማድረግ በፈለገች ጊዜ ለዑምራ ኢህራም እንድታደርግ እህትህን ያዝና ከሐረም ክልል ዉጭ ዉጣ ብለዉ አዘዉታል፡፡

**ومن كان طريقه يمينا أو شمالا من هذه المواقيت فإنه يحرم إذا حاذى أقرب المواقيت إليه فإن لم يحاذ ميقاتا مثل أهل سواكن في السودان ومن يمر من طريقهم فإنهم يحرمون من جدة .**

ለኢሕራም በተከለሉ ቦታዎች በግራና በቀኝ አቅጣጫ አቋርጠዉ ለሚመጡ ሰዎች ከተከለሉት ቦታዎች ለነሱ በጣም በሚቀርቧቸዉ አቅጣጫ ሲደርሱ ኢህራም ማድረግ አለባቸዉ በግራና በቀኝ አቅጣጫ ለኢህራም ከተከለሉ ቦታዎች ማንኛዉንም ማግኘትና መቅጣጨት ያልቻሉ ሰዎች ለምሳሌ ፡- ሱዳን ሀገር የሚኖሩና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም ማድረግ ያለባቸዉ ጂዳ ሲደርሱ ነዉ፡፡

**ولا يجوز لمن مر بهذه المواقيت وهو يريد الحج أو العمرة أن يتجاوزها إلا محرما وعلي هذا فإذا كان في الطائرة وهو يريد الحج أو العمرة وجب عليه الإحرام إذا حاذى الميقات من فوقه فيتأهب ويلبس ثياب الإحرام قبل محاذاة الميقات فإذا حاذاه عقد نية الإحرام فورا.**

ሐጅን ወይም ዑምራን ያሰበ ሰዉ እነኝህ ክልሎች(ሚቃቶች) ላይ ኢህራም ሳያደርግ ማለፍ አይፈቀድለትም ሐጅን ወይም ዑምራን በማሰብ በአዉሮፕላን የሚጓዝ ለኢህራም

በተመደቡ(በተከለሉ) ቦታዎች አቅጣጫ በሚደርስ ጊዜ ኒያ( ኢህራም [1] ) ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል እነኝህ ክልሎች ሳይደርስ የኢህራም ልብሱን በመልበስ በቅድሚያ ይዘጋጅ በነሱ አቅጣጫ ሲደርስ በፍጥነት የኢህራምን ኒያ ማሰብ (መነየት) አለበት፡፡

ولا يجوز له تأخيره إلي الهبوط في جدة لأن ذلك من تعدى حدود الله تعالى

(ومن يتعد حدود الله فقد ظلم نفسه ) سورة الطلاق 1 ) (ومن يتعد حدود

الله فأولئك هم الظالمون ) سورة البقرة 229 ) (ومن يعص الله ورسوله

ويتعد حدوده يدخله نارا خالدا فيها وله عذاب مهين) سورة النساء 14 )

ኢህራሙን አዉሮፕላኑ ጅዳ እስከሚያርፍ ድረስ ማቆየት አይቻልም ይህን ማድረግ የአላህን ወሰኖች ከመተላለፍ ይመደባል አላህ ﷻ እንድህ ብሏል ﴾የአላህን ወሰኖች የተላለፈ ራሱን በድሏል﴿አጥጦላቅ 1 ﴾የአላህን ሕግ የሚተላለፍ እነርሱ በደለኞች ናቸዉ﴿አል-በቀራህ 229 ﴾አላህንና መልዕክተኛዉን ያልታዘዘ ወሰኖችን የጣሰም እሳትን ያስገባዋል፡፡ ከዉስጧም ዘወትር ይኖራል ፡፡አዋራጅ የሆነ ቅጣት ይጠብቀዋል﴿ ፡፡ ( አኒሳዕ 14 )

ومن مر بالمواقيت وهو لا يريد حجا ولا عمرة ثم بدا له بعد ذلك أن يعتمر

أو يحج فإنه يحرم من المكان الذي عزم فيه علي ذلك لأن في الصحيحين من

حديث ابن عباس رضي الله عنهما في ذكر المواقيت قال ومن كان دون ذلك

فمن حيث أنشأ وإذا مر بهذه المواقيت وهو لا يريد الحج ولا العمرة وإنما

---

ኢህራም፡-ማለት ሐጅ ወይም ዑምራ ስነ-ስርዓት ዉስጥ መግባትን መነየት ነዉ [1]

يريد مكة لغرض آخر كطلب علم أو زيارة قريب أو علاج مرض أو تجارة أو نحو ذلك فإنه لا يجب عليه الإحرام إذا كان قد أدى الفريضة ،لحديث ابن عباس السابق وفيه "هن لهن ولمن أتي عليهن من غير أهلهن لمن كان يريد الحج والعمرة فإن مفهومه أن من لا يريدهما لا يجب عليه الإحرام.

ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ሳያስብ በኢህራም ክልሎች ላይ ያለፈ ካለፈ በኋላ ሐጅ ወይም ዑምራ ማድረግ ከፈለገ መስራት አለብኝ ብሎ እወሰነበት ቦታ ላይ ኒያ (ኢህራም) ያድርግ  ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ሳያስብ በኢህራም ክልሎች ላይ ያለፈ መካ መሄድ የፈለገዉ ለሌላ ጉዳይ ከሆነ (ለምሳሌ) እዉቀት ፍለጋ፣ ቤተሰብ ለመጠየቅ ፣ ለህክምና ፣ ለንግድና ለሌላም ነገር ይሁን  ከአሁን በፊት ሐጅ አድርጎ ከሆነ ኢህራም ማድረግ ግዴታ አይሆንበትም፡፡

وإرادة الحج والعمرة غير واجبة علي من أدي فريضتهما وهما لا يجبان في العمر إلا مرة واحدة لقول النبي صلي الله عليه وسلم حين سئل هل يجب الحج كل عام؟ قال "الحج مرة فما زاد فهو تطوع" والعمرة كالحج لا تجب إلا مرة في العمرة لكن الأولي لمن مر أن لا يدع الإحرام بعمرة أو حج إن كان في أشهره وإن كان قد أدى الفريضة ليحصل له بذلك الأجر ويخرج من الخلاف في وجوب الإحرام عليه.

ለሐጅ ወይም ለዑምራ ኒያ(ኢህራም) ማድረግ ሐጅና ዑምራ በሰራ ሰዉ ላይ ግዴታ አይደለም  ሐጅና ዑምራ  በሰዎች ላይ ግዴታ የሚሆኑት በዕድሜ (በሕይዎት) አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ነቢዩ ﷺ ሐጅ በሰዎች ላይ በየዓመት ሁል ጊዜ ግዴታ ይሆናልን ? ተብለዉ ተጠየቁ  ነቢዩ ﷺ በዕድሜ አንድ ጊዜ

ብቻ ነዉ ከአንድ በላይ የሚጨምር ካለ ትርፍ ነዉ በማለት መልሰዋል፡፡ እንዲሁ ዑምራም ከሐጅ ጋር ተመሳሳይ ነዉ በዕድሜ አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ግዴታ የሚሆነዉ፡፡
ነገር ግን በነኚህ ለኢህራም በተከለሉ (በተመደቡ) ቦታዎች ላይ ለሚያልፍ ሰዉ ለዑምራም ሆነ ከአሁን በፊት ሐጅ ያደረገ ቢሆንም እንኳ የሐጅ ወራት ገብቶ ከሆነ ለሐጅ አጇር እንዲፃፍለትና ለኢህራም በተመደቡ ክልሎች አጠገብ ምን ጊዜም ባለፈ ቁጥር ማንኛዉም ሰዉ ኢህራም ማድረግ ግዴታ ነዉ የሚል ዉዝግብ ስላለ ከዚህ ለመዉጣት ሲባል ኢህራም አድርጎ ማለፉ በደረጃ ይበልጣል፡፡

**أنواع الأنساك ثلاثة**

**الأول التمتع بالعمرة إلي الحج وهو أن يحرم في أشهر الحج بالعمرة وحدها ثم يفرغ منها بطواف وسعي وتقصير ويحل من إحرامه ثم يحرم بالحج في وقته من ذلك العام.**

## <u>የሀጅ ስራ አፈፃፀም ሂደት ለሶስት ይከፈላል</u>

* የመጀመሪያዉ (አት-ተመቱዕ) ዑምራ አድርጎ እስከ ሐጅ ድረስ ነፃ መሆን ተመቱዕ ማለት በሐጅ ወራት [1] ለዑምራ ብቻ ኒያ (ኢህራም) በማድረግ ከዚያም የኡምራን ስራ ከዕባን በመዞር ፣ በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ በማድረግና ፀጉሩን በማሳጠር እንደጨረሰ ከኢህራሙ ይፈታ(ወደ መደበኛ አኗኗሩ ይመለስ) ፡፡ በዚያዉ አመት ዙል ሂጃ ስምንት ላይ( የዉመ-አተርዊያ ) ለሀጅ ኒያ (ኢህራም ) ማድረግ ነዉ፡:

---

[1] ትክክለኛዉ የሐጅ ወራት የሚባሉት ከሸዋል ወር መጀመሪያ አንስቶ እስከ ዙል ሂጃ ወር መጨረሻ ድረስ ያሉት ጊዜያት ናቸዉ

**الثاني :القران ،وهو أن يحرم بالعمرة والحج جميعا ،أو يحرم بالعمرة أولا ثم يدخل الحج عليها قبل الشروع في طوافها فإذا وصل إلي مكة طاف طواف القدوم،وسعي بين الصفا والمروة للعمرة والحج سعيا واحدا ثم استمر علي إحرامه حتى يحل منه يوم العيد.ويجوز أن يؤخر السعي عن طواف القدوم إلي ما بعد طواف الحج ،لا سيما إذا كان وصوله إلي مكة متأخرا وخاف فوات الحج إذا اشتغل بالسعي .**

* ሁለተኛዉ አል ቂራን ይባላል አልቂራን ማለት በሐጅ ወራት ዑምራንና ሐጅን በማጣመር በአንድ ላይ መነየት (ኢህራም) ማድረግ ወይም(ቂራን ማለት)በሐጅ ወራት ዑምራን ኒያ(ኢህራም) አድርጎ ከገባ በኋላ ከዚያም የኡምራዉን ጦዋፍ ከመጀመሩ በፊት(በተለያዩ ምክንያቶች የሀጅ ኒያን በዑምራ ላይ ማካተት ነዉ፡፡ መካ እንደደረሰ የመግቢያ ጦዋፈ(ጦዋፈ ልቁዱም)ያደርጋል በሶፋና በመርዋ መካከልም ለዑምራና ለሀጅ አንድ ጊዜ ብቻ (ማለት ሰባት ጊዜ)ምልልስ ያደርጋል ከዚያም እስከ ኢድ ቀን(ዙልሂጃ 10) እስከሚደርስ በኢህራም ላይ መቆየትአለበት ፡፡ የመግቢያ የሆነዉን ጦዋፍ ከጨረሰ በኋላ በሶፋና በመርዋ መካከል የሚያደርገዉን ምልልስ ለጦዋፈል ኢፋዳ(የኢድ ቀን ወይም በሌላ ቀን ከዕባን ) እስከሚዞር ድረስ ማቆየት ይቻላል . በተለይም አንድ ሰዉ መካ ሲደርስ የዘገየ ሆኖ ከደረሰ በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ ካደረኩ ሀጅ ያመልጠኛል ብሎ የሚፈራ ከሆነ ፡፡

**الثالث : الإفراد وهو أن يحرم بالحج مفردا فإذا وصل مكة طاف طواف القدوم وسعي للحج واستمر علي إحرامه حتى يحل منه يوم العيد. ويجوز**

**أن يؤخر السعي إلي ما بعد طواف الحج كالقارن وبهذا تبين أن عمل المفرد والقارن سواء إلا أن القارن عليه الهدي لحصول النسكين له دون المفرد .**

* ሶስተኛዉ ኢፍራድ ይባላል. አልኢፍራድ ማለት በሐጅ ወራት ለሐጅ ብቻ ኒያ (ኢህራም) ማድረግ ነዉ መካ እንደደረሰ የመግቢያ ጦዋፌ (ጦዋፌልቁዱም) እና የሐጅን ሰዕይ ( በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ) ያደርጋል፡፡ ከኢህራሙ ሳይፈታ የኢድ ቀን (ዙል ሂጃ 10) እስከሚደርስ መቆየት አለበት ፡፡የሐጅን ሰእይ ከሚና መልስ ማድረግ ይቻላል እዚህ ላይ የምንረዳዉ ሀጅ ብቻ ለማድረግ ኒያ ያደረገ እና ሐጅና ዑምራን አጣምሮ ለመስራት ኒያ (ኢህራም) ያደረገ ተመሳሳይ ስራ እንደሚሰሩ እንረዳለን ነገር ግን ቃሪን ሁለት ስራዎችን ባንድ ጊዜ ስለሰራ ማረድ አለበት፡፡ (<u>ሙፍሪድ) ለሐጅ ብቻ ኒያ ያደረገ ማረድ የለበትም፡፡</u>

**وأفضل هذه الأنواع التمتع لأن النبي صلي الله عليه سلم أمر به أصحابه وحثهم عليه بل أمرهم أن يحولوا نية الحج إلي العمرة من أجل التمتع، فعن ابن عباس رضي الله أنه سئل عن متعة الحج ؟ فقال "أهل المهاجرون والأنصار وأزواج النبي صلي الله عليه وسلم في حجة الوداع وأهللنا ،فلما قدمنا مكة قال النبي صلي الله عليه وسلم " اجعلوا إهلالكم بالحج عمرة إلا من قلد الهدي " فطفنا بالبيت وبالصفا والمروة وأتينا النساء ولبسنا الثياب رواه البخاري**

ከሶስቱ የሐጅ መፈፀሚያ መንገዶች በደረጃ ተመቱዕ በላጭ ነዉ ምክንያቱም ረሱልﷺ ባልደረባዎቻቸዉን ያዘዟቸዉና የመረጡላቸዉ ተመቱዕን ነበርና ለዚህም ነዉ ሀጅ ብቻ

ለማድረግ ኒያ (ኢህራም) አድርገዉ የነበሩትን ወደ ዑምራ እንዲቀይሩ ያዘዟቸዉ፡፡ ኢብኑ አብባስ ﵁ ስለሀጅ ሙተአ ተጠየቀ ሙሀጅሮች ፤ አንሷሮች፤ የረሱል ﷺ ሚስቶችና እኛም ሀጅ ብቻለማድረግ ኒያ አደረግን መካ እንደገባን ረሱል ﷺ ሐጅ ብቻ ለማድረግ ኒያ አድርጋችሁ የነበረዉን ወዴ ዑምራ ቀይሩት አሉ ወዴ አላህ ለመቃረብ የሚሰዋ እንሰሳ የያዘ ሲቀር ከዕባን እንዲሁም በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ አደረግን ከሚስቶቻችን ጋር ግንኙነት ፈፀምን ማንኛዉንም ልብስ ለበስን ብሏል (ቡኻሪ የዘገቡት )

ومتي عدم المتمتع والقارن الهدي أو ثمنه بحيث لا يكون معه من المال إلا ما يحتاجه لنفقته ورجوعه فإنه يسقط عنه الهدي ويلزمه الصوم لقوله تعاتي (فمن تمتع بالعمرة إلي الحج فما استيسر من الهدي فمن لم يجد فصيام ثلاثة أيام في الحج وسبة إذا رجعتم تلك عشرة كاملة )

ሙተመቲዑ ወይም ቃሪኑ የሚያርደው(የሚሰዋው) ካጣ እንዲሁም የሚገዛበት ብር ካላገኘ ብር ቢኖረዉም ለቀለብና ለሀገሩ መመለሻ የሚፈልገዉ ከሆነ ማረድ ግዴታ አይሆንበትም ፡፡ ፆም ይፁም አላህ እንዲህ ብሏል፡- (እስከ ሐጅ ድረስ በዑምራ የተጣቀመ ከሀድይ የቻለዉን (ለመስዋዕትነትያቅርብ) ይህን ያላገኘ በሐጅ ወራት ሶስት ቀናትን(ወደ ቤተሰቦቻችሁ) ስትመለሱ ደግሞ ሰባት ቀናትን ይፁም (ሀድይን የሚተኩና የተሟሉ )አስር ቀናት ይሆናሉ ፡፡

ويجوز أن يصوم الأيام الثلاثة في أيام التشريق وهي اليوم الحادي عشر والثاني عشر والثالث عشر من ذي الحجة لقول عائشة وابن عمر رضي الله عنهم "لم يرخص في أيام التشريق أن يصمن إلا لمن لم يجد الهدي" رواه

**البخاري ويجوز أن يصومها قبل ذلك بعد الإحرام بالعمرة إذا كان يعرف من نفسه أنه لا يستطع الهدي لقول النبي صلي الله عليه وسلم "دخلت العمرة في الحج إلي يوم القيامة "فمن صام الثلاثة في العمرة فقد صامها في الحج لكن لا يصوم هذه الأيام يوم العيد لحديث أبي سعيد رضي الله عنه أن النبي صلي الله عليه وسلم "نهى عن صوم يومين : يوم الفطر ويوم النحر" متفق عليه**

ሶስቱን ቀናት በአያምትተሽሪቅ ቀናት ዉስጥ መፆም ይችላል እነኝህ ቀናት ከዙል ሂጃ አ11ኛዉ ፤ አ12ኛዉና አ13ኛዉ ናቸዉ ። አኢሻና ኢብኑ ኡመር ﵁ ፡-አያመትተሽሪቅ መፆም አይቻልም ሀድይ (የሚሰዋዉ) ያላገኘ ሰዉ ሲቀር ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ የዘገቡት) ከነኝህ ቀናት በፊት መፆም ይችላል ለዑመራ ኒያ( ኢህራም) ካደረገ በኃላ ማረድ እንደማይችል እርግጠኛ ከሆነ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ፡- ዑምራ ቂያማ ቀን ድረስ ከሐጅ ዉስጥ ገብታለች ብለዋል ። ሶስቱን ቀናት ለዑመራ ኒያ( ኢህራም) ካደረገ በኃላ የፆመ በእርግጥ ሐጅ ዉስጥ እንደፆመ ነዉ፡፡ ነገር ግን እነኝህን ቀናት የኢድ ቀን(ዙልሂጃ 10) መፆም አይቻልም፡፡ አቡ ሰዒድ ﵁ ረሱል ﷺ ሁለት ቀናትን ከመፆም ከልክለዋል ዒድ አልፈጥርና ከዙል ሂጃ አ 10ዉን ቀን ብሏል ።( ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት )

**ويجوز أن يصوم هذه الثلاثة متوالية ومتفرقة ولكن لا يؤخرها عن أيام التشريق وأما السبعة الباقية فيصومها إذا رجع إلي أهله إن شاء متوالية وإن شاء متفرقة لأن الله سبحانه أوجبها ولم يشرط أنها متتابعة.**

እነኚህን ሶስት ቀናት አከታትሎም ሆነ ለያይቶ መፆም ይችላል ግን ከአያመትተሸሪቅ ማዘግየት አይችልም ሌሎቹን ሰባት ቀናት ወደ ቤተሰቦቹ ሲመለስ ከፈለገ አከታትሎ ወይም ለያይቶ መጾም ይችላል፡፡ አላህ ፆምን ግዴታ አደረገ እንጅ በተከታታይ መፆም አለበት የሚል መስፈርት አላስቀመጠም፡፡

**فأما نوع الهدي فهو من الإبل أو البقر أو الغنم الضأن والمعز لقوله تعالي (ولكل أمة جعلنا منسكا ليذكروا اسم الله علي ما رزقهم من بهيمة الأنعام ) (الحج 34 ) وبهيمة الأنعام هي الإبل والبقر والغنم وتجزيء الواحدة من الغنم في الهدي عن شخص واحد. وتجزيء الواحدة من الإبل أو البقر عن سبعة أشخاص لحديث جابر رضي الله عنه قال "أمرنا رسول الله صلي الله عليه وسلم أن نشترك في الإبل والبقر كل سبعة منا في بدنة "متفق عليه**

የሐድዩ(የሚሰዋዉ) አይነት ግመል፣ ከብት፣ በግና ፍየል ናቸዉ፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-( ለሁሉም ህዝቦች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ደንግገናል የአላህን ስም ከለማዳ እንስሳት በለገሳቸዉ ሲሳይ ያወሱት ዘንድ (ይህን አደረግን) (አል-ሐጅ34) ለማድ እንስሳት የሚባሉት ግመል ከብት ፍየል እና በግ ናቸዉ አንድ ፍየል ወይም በግ ለአንድ ሰዉ በቂ ነዉ አንድ ግመል ወይም ከብት ለሰባት ሰዎች በቂ ነዉ፡፡ ጃቢር ﵁ ረሱል ﷺ ግመል ወይም ከብት ላይ ሰባት ሰዎች እንዲጋሩ አዘዉናል ብሏል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል)

**فيجب أن يتوافر فيه شيئان**

1. **بلوغ السن الواجب وهو خمس سنين في الإبل وسنتان في البقر وسنة في المعز وستة أشهر في الضأن فما دون ذلك لا يجزيء لقول النبي صلي الله**

**عليه وسلم "لا تذبحوا إلا مسنة إلا أن يعسر عليكم فتذبحوا جذعه من الضأن "رواه الجماعة إلا البخاري**

የሚታረደዉ እንስሳ ሁለት ነገሮች ያሟላ መሆን አለባቸዉ
1. ግመል ከሆነ አምስት ዓመት የሞላዉ መሆን ከብት ሁለት አመት ፍየል አንድ ዓመት በግ ስድስት ወር ከነዚህ ዕድሜ ያነሰ ከሆነ አይቻልም ረሱል ﷺ እንዳታርዱ አምስት ዓመት የሞላት ግመል ካልሆነች በስተቀር ይህችን ግመል ማግኘት ካልቻላችሁ ስድስት ወር የሞላዉ በግ ማረድ ትችላላችሁ ብለዋል ፡፡(ቡኻሪ ሲቀሩ ሌሎቹ የዘገቡት)

**2. السلامة من العيوب الأربعة التي أمر النبي صلي الله عليه وسلم باتقائها وهي .العوراء البين عورها .المريضة البين مرضها .العرجاء البين ضلعها . الهزيلة التي لا مخ فيها**

2. ረሱል ﷺ እንድንርቃቸዉ ያዘዙን ከሆኑት አራት ነዉሮች ያገለለ መሆን ፡፡ የዓይኗ መጥፋት ግልፅ የሆነ. በግልፅ የሚታይ በሽታ መኖር. የተሰበረች መሆን .የከሳች መሆን

**وأما مكان ذبح الهدي ففي منى ويجوز في مكة وفي بقية الحرم لقول النبي صلي الله عليه وسلم "كل فجاج مكة منحر وطريق"رواه أبو داود**

**وعلي هذا فإذا كان ذبح الهدي بمكة أفيد وأنفع للفقراء فإنه يذبح في مكة إما في يوم العيد أو في الأيام الثلاثة بعده ومن ذبح الهدي خارج حدود الحرم في عرفة أو غيرها من الحل لم يجزئه علي المشهور**

<u>ሀድዩ የሚታረድበት ቦታ ሚና</u> ፤ መካና ሀረም ነዉ ረሱል ﷺ መካ የሚገኙ መንገዶች በሙሉ እነሱ ላይ ማረድ እንዲሁም ወደ መካ መግቢያ ማድረግ ይፈቀዳል ብለዋል፡፡(አቡዳዉድ

ዘግበዉታል)መካ መታረዱ ለድሆች በጣም ጠቃሚ ነዉ መካ ሲታረድ የዒድ ቀን ወይም ከዒድ በኃላ ባሉት ሶስት ቀናት ዉስጥ ስለሆነ ለድሆች በጣም ጠቃሚ ነዉ ሀድዩን ከሀረም ክልል ዉጭ ያረደ ለምሳሌ አረፋ ላይ ወይም ሌላ ቦታ ግልፅ በሆነዉ ንግግር እንዳላረደ ነዉ የሚቆጠረዉ፡፡

وأما وقت الذبح فهو يوم العيد إذا مضى قدر فعل الصلاة بعد ارتفاع الشمس قدر رمح إلي آخر أيام التشريق لأن النبي صلي الله عليه وسلم نحر هديه ضحى يوم العيد ويروى عنه صلي الله عليه وسلم أنه قال "كل أيام التشريق ذبح" فلا يجوز تقديم ذبح هدي التمتع والقران علي يوم العيد لأن النبي صلي الله عليه وسلم لم يذبح قبل يوم العيد وقال :"خذوا عني مناسككم" وكذلك لا يجوز تأخير الذبح عن أيام التشريق لخروج ذلك عن أيام التشريق ويجوز الذبح في هذه الأيام الأربعة ليلا ونهارا، ولكن النهار أفضل

የሚታረድበት ጊዜ የዒድ ቀን ፀሃይ ከፍ እንዳለች ሶላት የሚሰገድበት መጠን ካለፈ ጀምሮ አያመትተሽሪቅ መጨረሻ ድረስ ነዉ ረሱል ﷺ የኢድ ቀን ረፋድ ላይ ነዉ ያረዱት አያመትተሽሪቅ በሙሉ ማረድ ይቻላል የሚልም ሐዲስም አለ የቂራንና የተመቱዕ ሐድይን ከዒድ ቀን በፊት ማረድ አይፈቀድም ረሱል ﷺ ከዒድ ቀን በፊት አላረዱም ረሱል ﷺ ሐጅ ላይ የምትሰሯቸዉን ስራዋች ከኔ ያዙ ብለዋል እንዲሁም ከአያመትተሽሪቅ ማሳለፍ አይቻልም፡፡
በነኝህ አራት ቀናት ዉስጥ ቀን ሌሊት ማረድ ይቻላል ግን ቀን መሆኑ በደረጃ የበለጠ ነዉ፡፡

**وأما كيفية ذبح الهدي فالسنة نحر الإبل قائمة معقولة يدها اليسرى فإن لم يتيسر نحرها قائمة فباركة والسنة في غير الإبل الذبح مضطجعة علي جنبها**

*ሀድዩ መታረድ ያለበት ሁኔታ ግመል ከሆነ ች ግራ እጇን ታስራ እንደቆመች ይህ ካልተቻለ እንደተንበረከከች ማረድ ይቻላል ከግመል ውጭ ያሉ እንስሶች ከሆኑ በጎናቸዉ ከተኙ በኃላ ነዉ መታረድ ያለባቸዉ*

**ولا بد من قول الذابح بسم الله عند الذبح فلا تؤكل الذبيحة إذا لم يذكر اسم الله عليها لقوله تعالي (ولا تأكلوا مما لم يذكر اسم الله عليه وإنه لفسق) ( الأنعام 121) ولا تجزيء عن الهدى حينئذ لأنها ميتة لا يحل أكلها**

*የሚያርድ ሰዉ በሚያርድ ጊዜ ቢስሚላ ማለት ግደታ ነዉ የሚታረደዉ እንስሳ የአላህ ስም ካልተወሳበት ሃላል ሊሆን አይችልም(በከት ነዉ) አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል፡-( (ሲታረድ) የአላህ ስም ያልተወሳበትን (እንስሳ ሥጋ)አትመገቡ፡፡እርሱ አመፅ ነዉና)( አል-አንዓም 121)፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሀድዩ ተቀባይነት አያገኝም መመገብም አይቻልም በከት ነውና፡፡*

**محظورات الإحرام**

**محظورات الإحرام ما يمنع منه المحرم بحج أو عمرة وهي ثلاثة أقسام قسم محرم على الذكور والإناث. قسم محرم على الذكور فقط قسم محرم على الإناث فقط**

**<u>በኢህራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች</u>**

ማንኛዉም ሐጅ ወይም ዑምራ አድራጊ በኢህራም ወቅትየሚከለከላቸዉ ነገሮች ለሶስት ይከፈላሉ፡፡ በሁለቱም ፆታዎች ላይ ሐራም(ክልክል) የሆነ አለ በወንዶች ብቻ ክልክል የተደረገ አለ እንዲሁም በሴቶች ብቻ ሀራም የሆነ አለ

فأما المحرم على الذكور والإناث فهو:

1. إزالة شعر الرأس بحلق أو غيره(ولا تحلقوا رؤسكم حتى يبلغ الهدى محله) (البقرة 196 ) وألحق جمهور أهل العلم رحمهم الله تعالى شعر بقية الجسم بشعر الرأس وعلى هذا فلا يجوز للمحرم أن يزيل أي شعر كان من بدنه وقد بين الله سبحانه وتعالى فدية حلق الرأس بقوله (فمن كان منكم مريضا أوبه أذى من رأسه ففدية من صيام أو صدقة أو نسك ) وأوضح النبي صلي الله عليه وسلم أن الصيام مقداره ثلاثة أيام وأن الصدقة مقدارها ثلاثة آصع من الطعام لستة مساكين لكل مسكين نصف صاع وأن النسك شاة

<u>በሁለቱም ፆታዎች ላይ ሐራም የተደረገዉ</u> እርሱም፡-

1. የራስን ፀጉር በመላጨትም ይሁን በሌላ መንገድ ማስወገድ አላህ እንዲህ ብሏል፡-(ሐድይ ከሥፍራዉ እስከሚደርስ ድረስ ፀጉራችሁን አትላጩ) ፡፡( አል-በቀራህ 196) በርካታ ዑለማዎች መላ ሰዉነት ላይ የሚገኙ ፀጉሮችን ከራስ ፀጉር ጋር ተመሳሳይ ህግ አድርገዋል ስለዚህ ሙህሪም የሆነ ባጠቃላይ ከመላ ሰዉነቱ ላይ አንዲትንም ፀጉር ቢሆን እንኳ ማስወገድ አይችልም ፀጉሩን የላጨ ምን አይነት መቀጫ እንዳለበት አላህﷻ በማያሻማ መልክ ተናግሯል፡-

(ከመካከላችሁ በሽተኛ የሆነ ወይም ከራሱ ላይ ችግር ያለበት ሰዉ (ቢላጭ) የፆም፣ የምፅዋት ወይም የመስዋእት ቤዛ መክፈል ግድ ይሆንበታል )፡፡ ረሱል ﷺ ፆሙ ሶስት ቀናት እንደሆነም ምፅዋት ከሆነ ሰዎች ከሚመገቧቸዉ ሶስት ቁና ለስድስት ድሆች ለያንዳንዳቸዉ ግማሽ ቁና መስጠት መስዋዕት(እርድ) ከሆነ አንድ ፍየል (ወይም በግ)ማረድ እንደሆነ አብራርተዋል ፡፡

2. تقليم الأظافر أو قلعها ولا فرق بين أظفار اليدين والرجلين لكن لو انكسر ظفره وتأذى به فلا بأس أن يقص القدر المؤذى منه ولا فدية عليه

2.ጥፍርን መቁረጥ ወይም መንቀል እጅ ላይና እግር ላይ ያሉ ጥፍሮች ተመሳሳይ ናቸዉ ነገር ግን ጥፍሩ ተሰብሮ ከተቸገረ የሚያስቸግረዉን ብቻ መቁረጥ ይችላል (መቀጫ) ቤዛ የለበትም ፡፡

3. استعمال الطيب بعد الإحرام في ثوبه أو بدنه لقول النبي صلي الله عليه وسلم في المحرم الذي وقصته راحلته وهو واقف بعرفة "لا تقربوه طيبا "وعلل ذلك بكونه يبعث يوم القيامة ملبيا

3. ኢሕራም ላደረገ ሰዉ ኢሕራም ካደረገ በኋላ ሰዉነቱም ላይ ሆነ ልብሱ ሽቶ መቀባት አይፈቀድለትም ረሱል ﷺ ዓረፋ ቁሞ እያለ ግመሉ ስለገደለችዉ ሙሕሪም(ሶሃባ) ሽቶ እንዳትቀቡ ት ምክንያቱንም ሲገልፁ የቂያማ ቀን ለብበይክ እያለ ስለሚነሳ ብለዋል፡፡

4. عقد النكاح لقول النبي صلى الله عليه وسلّم: «لا يَنكح المحرم ولا يُنكح ولا يخطب» رواه مسلم. فلا يجوز للمُحرم أن يتزوج امرأةً ولا أن يعقدَ لها النكاحَ بولايةٍ ولا بوكالةٍ،

4. የጋብቻ ዉል መፈፀም ረሱል ﷺ ሙሕሪም ሰዉ አያገባም አይድርም ፣ አያጭምም ብለዋል(ሙስሊም የዘገቡት) ሙሕሪም የሆነ ሰዉ ማግባትና ለሴት ወልይ በመሆንም ይሁን ወኪል የጋብቻ ዉል መፈፀም አይፈቀድለትም።

5. المباشرةُ لشهوةٍ بتقبيل أو لمس أو ضمٍّ أو نحوه .

5. በስሜት ከሴት ጋር መነካካት፣ መሳሳምና መደባበስ አይፈቀዱም

6. الجماع لقوله تعالى: (فَمَنْ فَرَضَ فِيهِنَّ الْحَجَّ فَلا رَفَثَ وَلا فُسُوقَ وَلا جِدَالَ فِي الْحَجِّ) (البقرة: 197) الجماع أشد محظورات الإحرام تأثيراً على الحج وله حالان: الحال الأولى: أن يكون قبلَ التحللِ الأول فيترتب عليه شيئان:

1. وجوب الفدية وهي بَدنَة أو بقرة يذبحها ويُفرقها على الفقراء، ولا يأكل منها شيئاً.

2. فساد الحج الذي حصل فيه الجماع، لكن يلزم إتمامه وقضاؤه من السنة القادمة بدون تأخير ولا يفسدُ النُّسُكُ في باقي المحظورات.

الحال الثانية: أن يكونَ الجماع بعد التحلل الأول، أي بعد رمي جمرةِ العقبة والحلق، وقبل طواف الإفاضة، فالحج صحيح، لكن يلزمه شيئان

1. فديةٌ شاة يذبحها ويُفرقها جميعاً على الفقراء، ولا يأكل منها شيئاً.

2. أن يخرج إلى الحل، أي: إلى ما وراء حدود الحرم فيُجدد إحرامه، ويلبس إزراً ورداءً ليطوف للإفاضة مُحرماً.

6. ከሴት ጋር ግንኙነት መፈፀም አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል፡-( በነኝህ (ወራት) ዉስጥ ሐጅን በራሱ ላይ ግዳጅ ያደረገ  ሐጅ ዉስጥ ከሴት ጋር መገናኘት፣(በአላህ ላይ) ማመፅም፣ (ከባልደረቦቹ )ጋር መከራከርም የለበትም )፡፡ ከሴት ጋር መገናኘት ሐጃጅ(ሙሕሪም)ሊርቃቸዉ የሚገቡ  ከሆኑ ነገሮች ክልክልነቱ በጣም ጠንከር ያለ  ነዉ፡፡

<u>ከሴት ጋር መገናኘት  ሁለት ሁኔታዎች አሉት</u> ፡፡

የመጀመሪያዉ ግንኙነቱ የተፈፀመዉ ከመጀመሪያዉ ተሀሉል በፊት ከሆነ ሁለት ባህሪዎች አሉት እነሱም፡-

1. ግመል ወይም ከብት ማረድ ምንም ነገር ሳይመገብ ለድሆች ማከፋፈል

2. ሐጁ ዉድቅ ነዉ  ግን ማቋረጥ የለበትም ተጨማሪ በሚቀጥለዉ ዓመት ሳያዘገይ ቀዷ ማዉጣት ግዴታ ይሆንበታል. (ሐጅ ላይ ሙሕሪም ከሚከለከላቸዉ) ከግንኙነት ዉጭ ያሉት  ሐጅን ዉድቅ አያደርጉትም፡፡

*ሁለተኛዉ ሁኔታ ግንኙነቱ የተፈፀመዉ ከተሀሉለል አወል(ከመጀመሪያዉ መፈታት) በኋላ ከሆነ ማለት ጀምረተል አቀባ ላይ ጠጠር ከወረወረና ከተላጬ በኋላ ግን ከጦዋፈል ኢፋዷ በፊት  ሐጁ ትክክል ነዉ ነገር ግን ሁለት ነገሮች ግዴታ ይሆኑበታል፡፡

1. ፍየል (ወይም በግ) ማረድ ምንም ነገር ከስጋዉ ሳይመገብ ለድሆች ማከፋፈል .

2. ከሐረም ክልል  በመዉጣት ሽርጥና ጋቢ ለብሶ ኒያ (ኢህራም) በማደስ  ለኢፋዷ ጦዋፍ ማድረግ፡፡

7. من محظورات الإحرام: قتل الصيد،

7.ሙህሪም  ከሚከለከላቸዉ ነገሮች  የዱር አዉሬ ማደን፡፡

**وإذا قتل المُحرمُ الصيد متعمداً فعليه جزاؤه، لقوله تعالى: (وَمَنْ قَتَلَهُ مِنْكُمْ مُتَعَمِّداً فَجَزَاءٌ مِثْلُ مَا قَتَلَ مِنَ النَّعَمِ يَحْكُمُ بِهِ ذَوَا عَدْلٍ مِنْكُمْ هَدْياً بَالِغَ الْكَعْبَةِ أَوْ كَفَّارَةٌ طَعَامُ مَسَاكِينَ أَوْ عَدْلُ ذَلِكَ صِيَاماً) (المائدة: 95) فإذا قتلَ حمامة مثلاً فمثلها الشاة فيُخير بين أن يذبح الشاة ويُفرقها على الفقراء فديةً عن الحمامة، وبين أن يُقومها ويُخرج ما يقابل القيمة طعاماً للمساكين، لكل مسكين نصف صاع، وبين أن يصوم عن إطعام كل مسكين يوماً. وأما قطع الشجر فليس حراماً على المُحرم وإنما يَحرمُ على من كان داخل حدود الحرَمِ سواءٌ كان محرِماً أم غيرَ محرم، وعلى هذا يجوز قطع الشجر في عرفة للمُحرِم وغير المُحرِم، ويحرم في مزدلفة ومنى على المحرم وغير المحرم لأن عرفة خارجُ حدودِ الحرم، ومزدلفة ومنى داخل حدودِ الحرمِ.**

*ሙህሪም እያወቀ አዉሬ ከገደለ መቀጮ አለበት አላህ እንዲህ ብሏል፡- (ከናንተ እያወቀ ይህን የፈፀመ ከመካከላችሁ ፍትሃዉያን ሰዎች በሚሰጡት ብይን መሰረት የገደለዉን እንስሳ ምትክ ከቤት እንስሳዎች ከዕባ ደራሽ መስዋዕት ይተካል ፡፡ ወይም ድሆችን ያበላል አሊያም ይህን የሚመጥን ፆም ይፆማል )፡፡ ( አል-ማኢዳ፡95) ለምሳሌ፡- እርግብ ከገደለ ፍየል ምትክ ይሆናል ምርጫ ይሰጠዋል ፍየል አርዶ ለድሆች ማከፋፈል ወይም ፍየሏን በማስገመት በዋጋዋ ልክ ሰዎች ከሚመገቡት የአንድ ጊዜ ምግብ ለድሆች መስጠት*

ለያንዳንዱ ድሃ ያንድ ቁና ግማሽ [1] ወይም ድሆቹን መመገብ በመተዉ  በድሆቹ ቁጥር ልክ የመፆም ምርጫ አለዉ
<u>ዛፍ መቁረጥ በሙህሪም ላይ ሙህሪም ስለሆነ</u> አይደለም የሚከለከለዉ ከኢህራም ጋር የሚያገናኘዉ ነገር የለም፡፡ ሀራም የሚሆነዉ ሀረም ክልል ዉስጥ ባለ ሰዉ ላይ ነዉ ሙህሪም ቢሆንም ባይሆንም <u>ስለዚህ አረፋ ላይ ያለን ዛፍ ሙህሪም የሆነም ያልሆነም መቁረጥ ይችላል .ግን ሙዝደሊፋ እና ሚና ላይ ያሉ ዛፎች በሙህሪምም ላይ ሆነ ሙህሪም ባልሆነ ክልክል ናቸዉ፡፡ ምክንያቱም አረፋ ከሀረም ክልል ዉጭ ስለሆነ ሙዝደሊፋና  ሚና ሀረም ክልል ዉስጥ ስለሆኑ</u> ነዉ ፡፡

**فهذه المحظورات السبعة حرامٌ على الرجال والنساء.**

እነኚህ ሰባት ነገሮች በወንድም በሴት ላይ ክልክሎች ናቸዉ፡፡

**ويختص الرجال بمحظورين دونَ النساء وهما:**

1. **تغطية الرأس، لقول النبي صلى الله عليه وسلّم في المُحرِم الذي وقصته راحلته بعرفة: « ولا تُخَمِّروا رأسَه » ، متفق عليه.**

**فلا يجوز للرجل أن يُغطي رأسَه بما يلاصقه كالعمامة والطاقية ونحوذلك، فأما غير الملاصق كالشمسية وسقف السيارة والخيمة ونحوها فلا بأسَ به ولا بأس أن يحمل متاعه على رأسه  ولا بأسَ أن يغوص في الماء ولو تغطى رأسه بالماء.**

[1] 255.ግራም

2. مما يختص به الرجال من محظورات الإحرام لُبس المخيط، وهو أن يلبس ما يلبس عادةً سواء كان شاملاً للجسم كله، كالقميص، أو لجزء منه كالسراويل والفنايل والخفاف وشراب اليدين والرجلين، لحديث ابن عمر رضي الله عنهما أن النبي صلى الله عليه وسلّم سُئل: ما يلبس المُحرِم من الثياب؟ قال: «لا يلبسُ القميص ولا العمامة ولا البرانس ولا السراويل ولا الخفاف ولا ثوباً مسّه زعفرانٌ ولا ورس» متفق عليه.

لكن إذا لم يجد الإزار ولا ثمنه لبس السراويل، وإذا لم يجد النعلين ولا ثمنهما لبس الخفين ولا شيء عليه لقول النبي صلي الله عليه وسلم: «من لم يجد إزاراً فليلبس سراويل، ومن لم يجد نعلين فليلبس خُفين» متفق عليه. ولا بأس أن يلبس الخاتم وساعة اليد ونظارةَ العين وسماعة الأُذن،

<u>ወንዶችን ብቻ የሚመለከቱ ሁለት</u> ክልክል ነገሮች አሉ እነሱም፡-

1. ራስን መሸፈን ረሱልﷺ አረፋ ላይ ከግመሉ ወድቆ ስለሞተዉ ሶሃባ ‹‹ራሱን እንዳትሸፍኑ››ብለዋል(ቡኻሪ ሙስሊምየዘገቡት)ወንድ ራሱን በጥምጣምና በኮፊያ በሌላም ነገር መሸፈን አይችልም. ከራሱ ጋር የማይነካካ ከሆነ ዣንጥላ፣ የመኪና ጣራና ድንኳን ሌላም ነገር ቢሆን ችግር የለበትም፡፡ በራሱ ሻንጣዉን ቢሸከም ችግር የለበትም እንዲሁም ዉሃ ዉስጥ ቢገባ ራሱ በዉሃ ቢሸፈን እንኳ ችግር አያመጣም

2. ወንዶችን ብቻ ከሚመለከቱ ክልክል ነገሮች የተሰፋን ልብስ መልበስ ማለትም በተለምዶ የሚለበስ ልብስ ሰዉነቱን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ጀለቢያን ይመስል ወይም ከሰዉነቱ ከፊሉን የሚሸፍን ሱሪ፣ ፓንት ፣ኹፍ፣ የጅ ጓንትና የግር

ሹራብ  አብደላ ኢብኑ ኡመር ﵁ እንዳወሱት ረሱል ﷺሙህሪም ሰዉ ምን አይነት ልብስ ነዉ መልበስ ያለበት ተብለዉ ተጠየቁ   ጀለቢያ፣ጥምጣም፣ በራኒስ [1] ፣ሱሪ፣ኹፍና ማንኛዉንም ልብስ ዘዕፈራንና ወርስ በሚባል ቀለም የተነከረ መልበስ አይፈቀድለትም ብለዋል ::(ቡኻሪናሙስሊም የዘገቡት)ግን ሸርጥ ወይም የሚገዛበት ብር ከሌለዉ ሱሪ መልበስ ይችላል እንዲሁም ነጠላ ጫማ ወይም የሚገዛበት ብር ካላገኘ ሸፍን ጫማ ቢለብስ ችግር የለበትም  ረሱል ﷺ (ሸርጥ ያላገኘ ሱሪ ይልበስ ነጠላ ጫማ ያላገኘ ሸፍን ጫማ ይልበስ ብለዋል(ቡኻሪ ሙስሊም)ቀለበት  ሰዓት መነፀር የጆሮ ማዳመጫ ሙህሪም አይከለከልም ::

**وهذان المحظوران خاصان بالرجال، أما المرأة فلها أن تغطي رأسها، ولها أن تلبس في الإحرام ما شاءت من الثياب، غير أن لا تتبرج بالزينة، ولا تلبس القفازين، وهما شراب اليدين، ولا تنتقب ولا تُغطي وجهها إلا أن يمر الرجال قريباً منها فتغطي وجهها حيئنذٍ، لأنه لا يجوزُ كشفُ الوجه للرجال الأجانب أي غير المحارم.**

እነኝህ ሁለት ክልክል ነገሮች የሚመለከቱት  ወንዶችን ብቻ ነዉ. ሴት ግን ፀጉሯን መሸፈን አለባት ኢህራም ላይ የፈለገችዉን መልበስ ትችላለች  ግን ጌጦችን ግልፅ ማድረግ ፣ የጅ ጓንት፣ ኒቃብ መልበስና ፊቷን መሸፈን   አይፈቀድላትም ወንዶች ባካባቢዋ  በሚያልፉ ጊዜ ብቻ ሲቀር ይህ ከሆነ ግን ፊቷን መሸፈን አለባት  ሴት ፊቷን ዘመዶቿ ካልሆኑ በስተቀር እወንዶች ፊት መግለፅ ስለማይፈቀድላት::

---

ከራስ መሸፈኛ ጋር የተያያዘ የልብስ አይነት ነዉ [1]

**ويجوز للرجال والنساء تغيير ثياب الإحرام إلى غيرها مما لا يمتنعُ عليهما لُبسه حال الإحرام.**

ለሴትም ሆነ ለወንድ ኢህራም ባደረጉ ጊዜ የሚፈቀድላቸዉ የሆነን የልብስ አይነት መቀየር ይችላሉ፡፡

**<u>وإذا فعل المُحرم شيئاً من المحظورات السابقة</u> من الجماع أو قتلِ الصيد أو غيرهما فله ثلاث حالاتٍ:**

***<u>ሙህሪም ካለፉት ክልክል ነገሮች</u>*** አንዱን ቢፈፅም ለምሳሌ ፡- ግንኙነት ቢያደርግ አዉሬ ቢገድል ወይም ሌላ ነገር ቢፈጽም ሶስት ሁኔታዋች አሉት፡፡

**الأولى: أن يكون ناسياً أو جاهلاً أو مُكرَهاً أو نائماً، فلا شيء عليه، لا إثم ولا فدية ولا فساد نسك،فإن استمر عليه مع زوال العذر كان آثماً، مثال ذلك أن يُغطي المُحرمُ رأسه وهو نائم، فلا شيء عليه ما دام نائماً، فإذا استيقظ لزمه كشف رأسه فوراً، فإن استمر في تغطيته مع علمه بوجوب** كشفه كان آثما، وعليه ما يترتب على ذلك

የመጀመሪያዉ የፈፀመዉ እረስቶ ፣ ባለማወቅ ፣ ተገዶና ተኝቶ ከሆነ ምንም ነገር ወንጀልም ሆነ ቤዛም(ካሳ) የለበትም የሐጅ ስራዉ ዉድቅ አይሆንም ግን ምክንያቱ ከተወገደ በኋላ የሚቀጥል ከሆነ ወንጀለኛ ይሆናል ለምሳሌ፡- ሙህሪም ፀጉሩን ቢሸፍን የተኛ ሆኖ ምንም አይነት ነገር የለበትም ከእንቅልፉ ሲነሳ ቶሎ ፀጉሩን መግለፅ አለበት ፀጉሩን መግለፅ ግዴታ መሆኑን እያወቀ ራሱን በመሸፈን ላይ ከቀጠለ ወንጀለኛ ይሆናል ለጥፋቱም ቤዛ(መቀጫ) ይኖርበታል፡፡

**الثانية: أن يفعل المحظور عمداً لكن لِعُذرٍ يبيحُه، فعليه ما يترتب على فعل المحظور ولا إثم عليه لقوله تعالى: (فَمَنْ كَانَ مِنْكُمْ مَرِيضاً أَوْ بِهِ أَذىً مِنْ رَأْسِهِ فَفِدْيَةٌ مِنْ صِيَامٍ أَوْ صَدَقَةٍ أَوْ نُسُكٍ) (البقرة: 196)**

ሁለተኛዉ በቂ የሆነ ምክንያት እያለዉ ክልክል የሆነን ነገር እያወቀ ቢሰራ ክልክልን ያለምክንያት እያወቀ የፈፀመ ሰዉ ለጥፋቱ መቀጮ(ካሳ) ግዴታ እንደሚሆንበት ሁሉ ይህ ነገር እሱንም ይመለከተዋል ወንጀል ግን የለበትም አላህ ﷺ እንዲህ ብሏል፡-(ከመካከላችሁ በሽተኛ የሆነ ወይም ከራሱ ላይ ችግር ያለበትሰዉ (ቢላጭ)የፆም ፤ የምፅዋት ወይም የመስዋእት ቤዛ መክፈል ግድ ይሆንበታል )አል.በቀራ 196)

**الثالثة: أن يفعل المحظور عَمداً بلا عُذرٍ يبيحه، فعليه ما يترتب على فعله مع الإثم.**

ሶስተኛዉ ክልክል የሆነን እያወቀ ቢሰራ በቂ የሆነ ምክንያት ከሌለዉ ቤዛ(መቀጮ) አለበት መንጀለኛም ነዉ።

**<u>تنقسم محظورات الإحرام باعتبار الفدية إلى أربعة أقسام</u>:**

**أولاً: ما لا فدية فيه، وهو عقدُ النكاح.**

**ثانياً: ما فديته بدنة، وهو الجماع في الحج قبل التحلل الأول.**

**ثالثاً: ما فديته جزاؤه أو ما يقوم مقامَه، وهو قتل الصيد.**

**رابعاً: ما فديته صيامٌ أو صدقةٌ أو نُسكٌ حَسَب البيان السابق في فدية الأذى، وهو حلقُ الرأس.**

**وأَلْحَقَ به العلماء بقيةَ المحظورات سوى الثلاثة السابقة.**

<u>ኢህራም ላይ የሚከለከሉ ነገሮች</u> በቤዛ(በመቀጫ) ዙሪያ ለአራት ይከፈላሉ
*አንደኛዉ፡ ቤዛ(መቀጫ)የሌለበት እርሱም ጋብቻን መፈፀም
* ሁለተኛዉ፡ መቀጫዉ ግመል የሚሆንበት አለ እነሱም፡- ሐጅ ላይ ከመጀመሪያዉ መፈታት (ተሀሉል) በፊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም
* ሶስተኛዉ ፡ መቀጫዉ ከተገደለዉ አዉሬ ተመሳሳዩን(ከቤት እንስሳ) መሰል ከሌለዉ ደግሞ ዋጋዉን ይከፍላል እሱም፡- አዉሬ ማደን ነዉ
* አራተኛዉ ፡ መቀጫዉ ፆም ወይም ምፅዋት ወይም ምስዋዕት የሆነ አለ ባለፈዉ እንደተብራራዉ እርሱም ራስን መላጨት ነዉ፡፡
<u>ከዚህ ጋር(ማለት ከቁጥር አራት መቀጫ ጋር)</u> ያለፉት ሶስቱ ሲቀሩ ዐሊሞች ማንኛዉም ክልክል ነገር መቀጫዉ ተመሳሳይ ነዉ ብለዋል፡፡

**صفة العمرة**

**العمرةُ إحرامٌ وطوافٌ وسعيٌ وحلقٌ أو تقصيرٌ.فأما الإحرامُ فهو نية الدخول في النسك والسنة لمريده أن يغتسل كما يغتسل للجنابة، ويتطيب بأطيب ما يجد في رأسه ولحيته ولا يضرهُ بقاؤه بعد الإحرامِ والاغتسال عند الإحرام سُنَّةٌ في حق الرجال والنساء، حتى المرأة الحائض والنفساء،**

**ثم بعد الاغتسال والتطيب يلبس ثياب الإحرام، وهي للرجال إزارٌ ورداء، وأما المرأة فتلبس ما شاءت من الثياب غير أن لا تتبرج بزينة، ولا تنتقب ولا تلبس القفازين وتغطي وجهها عند الرجال غير المحارم.**

**<u>የዑምራ አፈፃፀም ስርዓት</u>**

ዑምራ ማለት፡- ኢህራም(ኒያ) ፣ ከዕባን ሰባት ጊዜ መዞር፣ በሶፋና በመርዋ መካከል ሰባት ጊዜ ምልልስ ማድረግ እና የራስ ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ነዉ፡፡ ኢህራም ማለት(ኢህራም ማድረጊያዉ ሥፍራ ላይ ሲደርስ) የዑምራን ስራ ለመስራት ኒያ ማድረግ ነዉ ዑምራን ላሰበ ሰዉ ገላዉን መታጠብ ሱና ነዉ ከሚያገኘዉ ሽቶ ጥሩ በሆነዉ ራሱን ና ፂሙን መቀባት ከኢህራም በኋላ የሽቶዉ ሽታ( ከሰዉነቱ ላይ) መገኘቱ አይጎዳዉም ኢህራም ላይ ገላን መታጠብ ለወንድም ሆነ ለሴት ሱና ነዉ የወር አበባ እና የወሊድ ደም የምታይ ሴት ብትሆን እንኳ (ገላን መታጠብ ሱና ነዉ) ከታጠበና ሽቶ ከተቀባ በኋላ የኢህራም (ሁለት) ልብሶችን መልበስ እነሱም፡- ሽርጥና ጋቢ(ፎጣ) ናቸዉ ሴት ግን የፈለገችዉን መልበስ ትችላለች ጌጦችን ግልፅ ማድረግ ፣ ኒቃብና የእጅ ጓንት መልበስ አይፈቀድላትም ፡፡ግን ዘመዶቿ ካልሆኑ ወንዶች አካባቢ በምትሆን ጊዜ ፊቷን መሸፈን አለባት

**ثم يُصلي غير الحائض والنفساء صلاةَ الفريضة إن كان في وقت فريضة، وإلا صلى ركعتين ينوي بهما سُنَّة الوضوء.**

**فإذا فرغ من الصلاة أحرمَ، وقالَ لبيك عمرة، «لَبَّيْكَ اللهُمَّ، لَبَّيْكَ، لَبَّيْكَ لَا شَرِيكَ لَكَ لَبَّيْكَ، إِنَّ الْحَمْدَ وَالنِّعْمَةَ لَكَ، وَالْمُلْكَ لَا شَرِيكَ لَكَ» هذه تلبية النبي صلى الله عليه وسلّم،**

**والسنة للرجال رفع الصوت بالتلبية لقول النبي صلى الله عليه وسلّم «أتاني جبريل فأمرني أن آمر أصحابي أن يَرفعوا أصواتهم بالإهلال والتلبية» أخرجه الخمسة.**

**وأما المرأة فلا ترفع صوتها بالتلبية ولا غيرها من الذكر لأن المطلوب في حقها التستر.**

ከዚያም የወር አበባና የወሊድ ደም የሚያዩ ሴቶች ሲቀሩ የፈርድ ሶላት ጊዜዉ ደርሶ ከሆነ ሶላት ይስገድ፡፡ ግን የፈርድ ሶላት ጊዜዉ ካልደረሰ ከዉዱእ በኋላ የሚሰገዱ ሁለት ረከዓን ኒያ በማድረግ ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ሶላት እንደጨረሰ <u>ለብበይክ ዑምረተን</u> በማለት ኒያ ( ኢህራም)ያድርግ ፡፡

ትርጉም ፡- ለዑምራ አቤት ብያለሁ ማለት ነዉ ከዚያም የሚቀጥለዉን ይጠቀም( <u>ለብበይክ</u> <u>አልላሁምመ ለብበይክ ለብበይክ ላሸሪከ ለከ ለብበይክ ኢንነል ሀምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ)</u>

ትርጉም ፡- ጌታዬ ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት እላለሁ ተጋሪ የለህም ምስጋና ፀጋና ንግስና ላንተ ብቻ ነዉ ሸሪካ የለህም ነቢዩ ﷺ ኢህራም ሲያደርጉ የተጠቀሙት ይህንን ነዉ፡፡<u>ወንዶች በተልቢያ(ለብበይክ</u> አልላሁምመ ለብበይክ በሚሉ ) ጊዜ ድምፃቸዉን ከፍ ማድረጋቸዉ ሱና ነዉ ምክኒያቱም ነቢዩ ﷺ ጅብሪል عليه السلام መጣና ባልደረባዋቼን በተልቢያና በላኢላሀ ኢለሏህ ድምፃቸዉን ከፍ ማድረግ እንዳለባቸዉ እዘዛቸዉ በማለት አዘዘኝ ብለዋል (አምስቱ ዘግበዉታል)

<u>ሴት ግን</u> በተልቢያም ሆነ በተለያዩ ዚክሮች ድምፅ ከፍ ማድረግ የለባትም ከሷ የሚፈለገዉ ድምፃን መቀነስ ስለሆነ ፡፡

**وإذا كان من يريد الإحرام خائفاً من عائق يمنعه من إتمام نُسكهِ؛ من مرض أو غيره، فإنه يُسن أن يشترط عند نية الإحرام، فيقول عند عقده: «إن حبسني حابس إِنَّ مَحِلِّي حَيْثُ حَبَسْتَنِي» ، وأما من لا يخاف من عائق**

يمنعه من إتمام نُسكه فلا ينبغي له أن يشترط، وينبغي للمُحرم أن يُكثر من التلبية خصوصاً عند تغير الأحوال والأزمان، مثل أن يعلو مرتفعاً، أو ينزل منخفضاً، أو يُقبل ليلٌ، أو نهار، أو يهمَّ بمحظور أو مُحرَّمّ .ويستمر في التلبية في العمرة من الإحرام إلى أن يشرعَ في الطواف وفي الحج من الإحرام إلى أن يرمي جمرة العقبة يومَ العيد. فإذا قَرُب من مكة سُنّ أن يغتسل لدخولها إن تيسر له، لأن النبي صلى الله عليه وسلّم كان يغتسل عند دخولها.

ወደ ሐጅ ሥርዓት ከገባ በኋላ በሆነ ችግር ምክኒያት በበሽታ ወይም በሌላ ነገር ኢህራሜን እፈታ ይሆናል የሚል ስጋት ከገባዉ የምፈታዉ ባገድከኝ ቦታ ላይ ነዉ በማለት ቅድመ ሑኔታ ማስቀመጥ ሱና ነዉ ነገር ግን ፍርሃት የሌለበት ሰዉ ይህን መስፈርት ማስቀመጥ የለበትም ሙህሪም ሰዉ ተልቢያ (ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ የሚለዉን ) ማብዛት አለበት በተለይም ሁኔታዎች እና ጊዜዎች በሚፈራረቁበት (በሚቀያየሩበት) ጊዜ ለምሳሌ፡- ከፍተኛ ቦታ ሲወጣ ዝቅተኛ ቦታ ሲወርድ ፣ ሌሊትና ቀን ሲፈራረቁ ፣ ክልክል የሆነን ነገር በአዕምሮዉ ባሰበጊዜ ዑምራ ከሆነ ኢህራም ካደረገ ጀምሮ ከዕባን መዞር እስከሚጀምር ድረስ ተልቢያን ማቋረጥ የለበትም ሐጅ ከሆነ ግን ኢህራም ካደረገ ጀምሮ የዒድ ቀን ጠጠር እስከ ሚወረዉር ድረስ ተልቢያን ማዘዉተር አለበት መካ ከተማ በሚቀርብ ጊዜ የሚመቸዉ ከሆነ ገላዉን መታጠብ ሱና ነዉ ነቢዩ ﷺ መካ መግባት ሲያስቡ ይታጠቡ ነበር፡፡

**فإذا وصل المسجد الحرامَ قدم رِجْلَه اليمنى لدخوله، وقال: «بِسْمِ اللَّهِ،والصلاة وَالسَّلَامُ عَلَى رَسُولِ اللَّهِ، اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذُنُوبِي وَافْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ أَعُوذُ بِاللَّهِ الْعَظِيمِ وَبِوَجْهِهِ الْكَرِيمِ وَسُلْطَانِهِ الْقَدِيمِ مِنْ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ» ويدخل بخشوع وتعظيم لله ، مُستحضراً بذلك نعمةَ الله عليه بتيسير الوصولِ إلى بيته الحرام.ثم يتقدم إلى البيت مُتّجهاً نحوَ الحجَرِ الأسود ليبتدىء الطوافَ، ولا يقول: نويت الطواف لأنه لم يَرِد عن النبي صلى الله عليه وسلّم. والنيةُ محلها القلب.**

ከተከበረዉ መስጊድ ሲደርስ ለመግባት ቀኝ እግሩን ያስቀድም ከዚያ (ቢስሚልላሂ ወስሶላቱ ወስሰላሙ አላ ረሱሊላሂ አልሏሁምመ ኢግፊር ሊ ዙኑቢ ወፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ አኡዙ ቢልሏሂ ልአዚም ወቢወጅሂሂ ልከሪም ወሱልጧኒሂ ልቀዲም ሚነ ሽሸይጧኒ ርረጂም) የሚለዉን ያንብብ ፡፡

ትርጉም፡- ባላህ ስም (እገባለሁ)የአላህ እዝነትና ሰላም በመለዕክተኛዉ ላይ ይዉረድ ጌታየ ሆይ ለወንጀሌ ምህረትህን ለግስልኝ የዝነትህን በር ክፈትልኝ ታላቅ በሆነዉ በአላህ ፣ በተከበረዉ ፊቱ እና መጀመሪያ የሌለዉ በሆነዉ ስልጣኑ ከአላህ እዝነት ከተባረረዉ ሰይጣን እጠበቃለሁ ማለት ነዉ፡፡ አላህን በመፍራትና ለአላህ ክብር የሰጠ ሆኖ ይግባ የተከበረ ወደሆነዉ ቤቱም (በይቱላህ) እንዲደርስ ነገሮችን ሁሉ በማግራት አላህ የለገሰለትን ፀጋ ያስታዉስ ከዚያም ቤቱን ለመዞር እንዲጀምር ሀጀረል አስወድ ባለበት አቅጣጫ ወደሀረሙ ይግባ ድምፁን ከፍ በማድረግ ነወይቱ አጥጦዋፍ ማለት አይቻልም (ቢድዓ ነዉ)

ከነቢዩ ﷺ አልተገኘም ኒያ ቦታው ልብ እንጅ ምላስ አይደለም ፡፡

فيستلم الحجرَ الأسودَ بيده اليمنى ويُقَبّله إن تيسّر له ذلك، يفعلُ ذلك تعظيماً لله، واقتداءً برسول الله صلى الله عليه وسلّم لا اعتقاداً أنّ الحجرَ ينفعُ أو يضرُّ، فإنما ذلك لله عز وجل عُمر بن الخطاب رضي الله عنه أنه كان يُقَبّل الحجَر ويقول: «إني لأعلم أنك حَجَر لا تضُرُّ ولا تنفعُ، ولولا أني رأيتُ رسولَ الله صلى الله عليه وسلّم يقبّلك ما قبّلتك» رواه الجماعة.

ከዚያም ሀጀረል አስወዱን በቀኝ እጁ ይንካዉ የሚችል ከሆነም ይሳመዉ ይህን ሲያደርግ ግን ለአላህ ﷻ ክብር እና የነቢዩን ﷺ አርአያነት ለመከተል እንጅ ይህ ድንጋይ ይጠቅማል ይጎዳል የሚል እምነት መኖር የለበትም ለምን ቢባል ጥቅምና ጉዳት የአላህ ብቻ ስለሆነ፡፡ ዑመር ኢብኑ ኸጧብ ؓ ድንጋዩን በሚስሙት ጊዜ እኔ አንተ መጥቀምም መጉዳትም የማትችል ድንጋይ መሆንህን አዉቃለሁ ነቢዩﷺ ሲስሙህ ባላያቸዉ ኖሮ አልስምህም ይሉ ነበር፡፡

فإن لم يتيسر له التقبيل، استلمه بيده وقبّلها، ففي «الصحيحين» من حديث ابن عمر رضي الله عنهما أنه استلم الحجَرَ بيدهِ ثم قبّل يده، وقال: ما تركتُه منذ رأيتُ النبي صلى الله عليه وسلّم يفعله.فإن لم يتيسر له استلامه بيده فلا يُزاحم، لأن الزحامَ يؤذيه، ويؤذي غيره، وربما حصل به ضرر، ولغوٌ وجدالٌ، ومقاتلةٌ. ويكفي أن يُشير إليه بيده ولو من بعيد، وفي «البخاري» من حديث ابن عباس رضي الله عنهما أن النبي صلى الله

**عليه وسلّم طاف بالبيت على بعير، كلما أتى على الركن أشار إليه. وفي روايةٍ: أشار إليه بشيء كانَ عنده وكبّر. ثم يأخذُ ذات اليمين، ويجعلُ البيتَ على يساره، فإذا وصل الركنَ اليماني استلمه إن تيسّر له بدون تقبيلٍ فإن لم يتيسر له فلا يزاحم.**

መሳም ካልቻለ ድንጋዩን በጁ በመንካት እጁን ይሳም አብደላ ኢብኑ ኡመር ﵁ እንዳወሱት ድንጋዩን በጁ ነካ ከዚያም እጁን ሳመ ይህን ነገር ነቢዩ ﷺ ሲሰሩት ካየሁ ጀምሬ ትቼዉ አላዉቅም ብሏል (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት) በጁ መንካት ካልቻለ ከሰዎች ጋር መጋፋት የለበትም መጋፋት ለራሱ ተቸግሮ በሌሎችም ላይ ችግርን መፍጠር ስለሆነ ፡፡ ጉዳት እንዲሁም ጥቅም የሌለዉ ነገር ፤ ክርክር እና መገዳደል ሊከሰትም ይችላል በሩቅ ቦታ ላይ እንኳ ቢሆን በጁ ማመላከት በቂ ነዉ ኢብኑ አብባስ ﵁ እንዳወሱት ነበዩ ﷺ ግመል ላይ ሆነዉ ቤቱን ዞሩ ሀጀረል አስወዱ አለበት አካባቢ ሲደርሱ በያዙት ነገር ወደ ሀጀረል አስወዱ በማመላከት አላህ አከበር አሉ ብሏል፡፡ (ቡኻሪ የዘገቡት ) ከዚያም የቀኝ አቅጣጫዉን በመያዝ ከዕባን በግራ አቅጣጫ በማድረግ (ከዕባዉን ይዙር) ሩክነል የማኒ ሲደርስ ከቻለ በጁ ይንካዉ ግን መሳም አይቻልም መንካት ካልቻለ መጋፋት የለበትም ( ሩክነል የማኒ ማለት ሀጀረል አስወድ ካለበት ማዕዘን በኋላ ሶስተኛዉ ማዕዘን ነዉ)

**ولا يستلم من البيت سوى الحجر الأسود والركن اليماني؛ ويقول بين الركن اليماني والحجَر الأسود: (رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ)**

**وكلّما مرَّ بالحجر الأسود فعل ما سبق وكبر ويقول في بقية طوافهِ ما أحبّ مِنْ ذكرٍ ودُعاء وقراءةٍ،**

ከዕባዉን በሙሉ  ከሐጀረል አስወዱና ከሩክነል የማኒ ዉጭ ማንኛዉንም በጅ መንካት አይፈቀድም   በሀጀረል አስወድና በሩክነል የማኒ መካከል በደረሰ ቁጥር  (ረብበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሀሰነተን ወቂና አዛበንናር)የሚለዉን ያንብብ፡፡

ትርጉም  ፡- ጌታችን ሆይ በቅርቢቱ ዓለም መልካም ነገርን በመጨረሻይቱም ዓለም መልካም ነገርን ለግሰን ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን ማለት ነዉ፡፡  በሀጀረል አስወድ አጠገብ ባለፈ ቁጥር መጀመሪያ ሲጀምር የሰራዉን ሁሉ መስራት አለበት አላህ አክበርም ይበል  ቤቱን በሚዞርበት ጊዜ ካለፉት ቦታዎች ዉጭ ላሉት ቦታዎች ከሆነ አላህን በማዉሳት ወይም እርሱን በመማፀን አልያም  ቁርአንን ማንበብ ይችላል፡፡

**والسنةُ  للرجل في هذا الطواف ـ أعني الطواف أول ما يَقدِمُ ـ أن يضطبعَ في جميع طوافهِ ويرملَ في الأشواطِ الثلاثةِ الأولى منه، دون الأربعةِ الباقيةِ. فأمّا الاضطباع فهو أن يُبرز كتفَه الأيمنَ، فيجعلَ وسطَ ردائهِ تحتَ إبطهِ وطرفيهِ على كتفهِ الأيسر.وأما الرَّمَلُ فهو: إسراعُ المشي مع مُقاربة الخُطا.والطواف سبعةُ أشواط، يبتدىء من الحجر الأسود وينتهي به.ولا يصحُّ الطوافُ من داخل الحِجْر.**

ወንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦዋፍ ሲያደርግ  መዞር ከጀመረ ጀምሮ ጦዋፉን እስከሚጨረስ (እስከሚያጠናቅቅ) ድረስ ኢድጢባዕ  መጠቀም  እና ከመጀመሪያዎቹ  ሶስቱ

ጦዋፎች(ዙሮች) ላይ ከመጨረሻዎቹ አራቶቹ ላይ ሳይሆን ረመል መጠቀም ሱና ነዉ

* ኢድጢባዕ ማለት ቀኝ ትካሻዉን ግልፅ ማድረግ ነዉ ጋቢዉን ከቀኝ ብብቱ ስር በማድረግ የጋቢዉን ሁለት ጫፎች ግራ ትካሻዉ ላይ ማድረግ

* ረመል ማለት እርምጃዎችን በማቀራረብ ፈጠን ብሎ መሄድ ማለት ነዉ   ቤቱ የሚዞረዉ ሰባት ጊዜ ነዉ ከሀጀረል አስወዱ ጀምሮ በሀጀረል አስወድ ይጨርስ  በሂጅሩ ዉስጥ ጦዋፍ ማድረግ አይቻልም

فإذا أتم سبعةَ أشواط، تقدم إلى مقام إبراهيم فقرأ (وَاتَّخِذُوا مِنْ مَقَامِ إِبْرَاهِيمَ مُصَلًّى وَعَهِدْنَا إِلَى إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ أَنْ طَهِّرَا بَيْتِيَ لِلطَّائِفِينَ وَالْعَاكِفِينَ وَالرُّكَّعِ السُّجُودِ ) (البقرة: 125) ثم يصلي ركعتين خلفَه قريباً منه إن تيسَّر، وإلا فبعيداً، يقرأ في الأولى بعد الفاتحة: (قُلْ يَا أَيُّهَا الْكَافِرُونَ) (الكافرون: 1) وفي الثانية بعد الفاتحة: (قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ) (الإخلاص: 1) ثم يرجع إلى الحجر الأسود فيستلمه إن تيسر له، وإلا فلا يشير إليه.

ሰባት ጊዜ ዙሮ ከጨረሰ በኃላ ወደ ኢብራሂም መቆሚያ በመሄድ ይኽን የቁርዓን አንቀፅ ያንብብ (ወትተኺዙ ሚን መቃሚ ኢብራሂመ ሙስሶለን ወአሂድና ኢላ ኢብራሂመ ወኢስማኢለ አንጠህሂራ በይቲየ ሊጦኢፊነ ወልአኪፊነ ወርሩከኢ ስሱጁድ)( አልበቀራ 125 ትርጉም ፡- ‹‹የኢብራሂምን መቆሚያ መስገጃ አድርጉ (በማለት ሰዎችን አዘዝን)፡፡ ወደ ኢብራሂምና (ልጃቸዉ)ኢስማዔልም ለጎብኚዎች ፤ ለተቀማጮች ፤ ለሩኩዕና ሱጁድ አድራጊዎችም ቤቱን አፅዱ የሚል ትዕዛዝ አስተላለፍን፡፡›› ከቻለ

ከኢብራሂም መቆሚያ (መቃሙ ኢብራሂም) ቀረብ ብሎ ከጀርባዉ ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ካልቻለ ግን ራቅ ብሎ ይስገድ ከፋቲሃ በኃላ ከመጀመሪያዉ ረከዓ ላይ ምዕራፍ ካፊሩን ያንብብ ሁለተኛዉ ረከዓ ላይ ሱረቱል ኢኽላስን ያንብብ፡፡ ከሰገደ በኋላ ወደ ሀጀረል አስወድ በመሄድ ከቻለ በጁ ይንካዉ፡፡ ግን በጁ መንካት ካልቻለ በጁም ሆነ በሌላ ነገር ማመላከት የለበትም፡፡

ثم يخرج إلى المسعى ليسعى، فإذا دنا من الصفا قرأ: ({إِنَّ الصَّفَا وَالْمَرْوَةَ مِنْ شَعَائِرِ اللَّهِ فَمَنْ حَجَّ الْبَيْتَ أَوِ اعْتَمَرَ فَلا جُنَاحَ عَلَيْهِ أَنْ يَطَّوَّفَ بِهِمَا وَمَنْ تَطَوَّعَ خَيْرًا فَإِنَّ اللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ (البقرة 158 } ولا يقرؤها في غير هذا الموضع. ثم يرقى على الصفا حتى يرى الكعبة، فيستقبلها ويرفع يديه فيحمد الله ويدعو بما شاء أن يدعو، وكان من دُعاء النبي صلى الله عليه وسلّم هنا «لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ، أَنْجَزَ وَعْدَهُ، وَنَصَرَ عَبْدَهُ، وَهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ» يُكررّ ذلك ثلاثَ مراتٍ، ويدعو بينها.

ከዚህ በኋላ ወደ ሶፋ (አልመስዓ ያምራ) ይዉጣ ከሶፋ ኮረብታ በሚቀርብ ጊዜ ይህን የቁርዓን አንቀፅ ያንብብ፡፡ (ኢንነ ስሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪ ልላሂ ፈመን ሀጅጀ ልበይተ አዊ እተመረ ፈላ ጁናሀ አለይሂ አን የጥጦወፈ ቢሂማ ወመን ተጦውወአ ኸይረን ፈኢንነ ልሏሀ ሻኪሩን አሊም ) (አልበቀራ 158)
ትርጉም፡- ሶፋና መርዋ ከአላህ (ትእዛዝ መፈፀሚያ )ምልክቶች መካከል (ሁለቱ) ናቸዉ፡፡ በሐጅ ወይም በዑምራህ ጊዜ (የአላህን )ቤት የጎበኘ ሰዉ በሁለቱ

